# የተሰደቡ ሰሞች

አመሰግናለሁ፡ ወንድም ኔቪል። ለእኔም—ድንቅ አጋጣሚ ነው። ዛሬ እዚህ መገኘት አይገባኝም ነበር። ቢሆንም፡ ዛሬ ማታ የጌታ እራት ይኖረናል፡ እናም ዛሬ ጠዋት ብሄድስ ብዬ አ—አሰብኩ። ስለዚህም ወንድም ኔቪልን ደወልኩለት፡ እሱም እንዲህ አለኝ፡ "ታዲያ፡ አሁን፡ መምጣትህ ካልቀረ፡" "ጥቂት ነገር ብትናገረንስ፡" አለኝ?

2 እኔም እንዲህ አሰብኩ፡ ምናልባት፡ ተሳክቶልኝ፡ ከሄድኩ፡ አልሰብክም፡ ነገር ግን በጥቂቱም ቢሆን ለቤተ ክርስቲያኒቱ እናገራለሁ፣ ማለቴ፡ ቤተ ክርስቲያንን ያበረታል ያልኩትን ነገር እናገራለሁ በማለት አሰብኩ።

3 ከመኸር የአደን ጉዞአችን ገና መ—መመለሣችን ነው፡ እኔን ጨምሮ እዚህ ካሉት ጥቂት ወንድሞች ጋር፡ በዚያ፡ ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል። ሁላችንም ረክተናል፡ እ—እጅግ ተደስተናል፡ አደን የወጣንበትን ዋናው ጨዋታችንን አ—አሸንፈናል። የአጋዘን ስጋ እጅግ—እጅግ ጥሩ እንደሆነ፡ እኔ እና ፓስተራችን እናውቃለን። በዚያም ጥሩ አጋዘን ያዝን። አንድ ድብ እና ሁለት አጋዘኖችን ያዝኩኝ። ተመልሰን መጥተናል።

4 እናም ይህ ጊዜ የመጨረሻዎቹ ሰባት ማኅተሞች የምሰብክበት ጊዜ ነው ተብሎ ይጠበቃል። በቤተ ክርስቲያን ግን በቂ ዝግጅት አላደረጉም። ይህ እንዲሆን ያደረገ፡ እንቅፋት የሆነባቸው፡ የሆነ ነገር አለ። ይህም፡ ቤተክርስቲያኒቱ ለምታዘጋጀው፡ ለሚመጡ እንግዶች የሚበቃ በቂ የመኪና ማቆሚያ ስፍራ ባለመኖሩ... ከተማው አስቸጋሪ ሆኖብናል።

5 እዚህ አዲስ ቤተክርስትያን መትከል እንፈልጋለን፡ ለዚያ የሚውል የምንመድበው በቂ ገንዘብ አለን፣ እ—እና—ትልቅ ቤተክርስቲያን ለማበጀት ነው። አገልግሎት በሚኖረን ጊዜ ሁሉ፡ እንደው፡ እናንተም ታውቁታላችሁ። በእውነት በጣም ያሳዝናል። ሰዎች በዝናብ ውስጥ፡ በግድግዳው አጠገብ ሲቆሙ፡ እ—እ—እጅግ ያሳቅቃል። ከጓደኞቼ እንኳን ሳይቀር ትችት ይደርሰብኛል። "ወንድም ብራንሃም እንደሚመስለኝ... " ብሎኛል፡ አንዱ ዶክተር ጓደኛዬ፡ እንዳለኝ፡ "ይኸውልህ ስፍራ ማግኘት ያለብህ ይመስለኛል።" "ሲያልፉ ሳያቸው፡ እጅግ አዝናለሁ፡" አለኝ።

6 አንዲት ነርስ ጎረቤቴ፡ እንዲህ አለችኝ፡ "ይኸውልህ፡ አንድ ቀን ጥዋት በአምስት ሰአት በዚያ አለፍሁ። አንተ ገና ወደዚያ አልመጣህም... " እንዲህ አለችኝ፡ "ህዝቡ ግን ገና ከጥዋቱ አምስት ሰዓት ላይ፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዙርያ ተሰብስቦ ነበር። አንተ የምትመጣው ግን ገና ዘጠኝ-ተኩል ላይ ነው። ስለዚህ፡ እዩት፡ እጅግ ከባድ ያደርግብኛል።

7 ለሁሉም የሚበቃ መቀመጫ ያለው፡ ሰፊ ቤተክርስቲያን እንዲኖረን እንፈልጋለን። እንደሚመስለንም በመጨረሻው ዘመን እየኖርን ነው፡ ብለንም እናምናለን። በዚህም ምክንያት... በአሁን ጊዜ ቅርጽ እየያዙ ስለሚገኙ፡ ስለ—ስለ—ስለእነዚህ ነገሮች ቤተ ክርስቲያኒቱን ማስተማር አለብን፡ ከዚህ በፊት በትንቢት የተነገሩት ነገሮች፡ አንዳንዶቹ፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ዓመታት ያስቆጠሩ

ናቸው። በተጨማሪም የዛሬ ሃያ-አምስት እና ሰላሣ አመታት፡ ከዚሁ ቤተ ክርስቲያን፡ የተነገሩ ትንቢቶች፡ ይፈጸማሉ። አሁንም እየተፈጸሙ ይገኛሉ። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ማሳሰብ አለብን፡ ነገር ግን በቂ ቦታ የለንም። ታዲያ ዛሬ ጠዋት...

8 የስልክ ጥሪዎቼን እና ሌሎች ነገሮቼን፡ ትላንትና ጨርሻለሁ፡ ዛሬ ከሰዓትም፡ የምደውላቸው ጥቂት ነገሮች፡ ወዘተረፈ ይኖሩኛል። እንዲሁም መግባት የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች አነጋግሬአለሁ፡ ሌላም በመስክ ላይ፡ የጭንቀት ህመም የገጠመው፡ የሚያምር ወጣት አገልጋይ ወንድማችን አለ። እንደዚህ የመሰሉ ብዙዎች አሉ፡ ከኖርዌ የመጣ ወንድምም አለ። እ—እና ከኋላ ባለው ኋለኛው ክፍል ውስጥ በትንሹ ቃለመጠይቆችን አድርገናል። ከዚያም እኔ "እንግዲህ፡ አሁን፡ መውጣት አለብን፡" አልኳቸው።

9 ወንድም ኔቪልም፡ "እሺ፡ ቤተክርስቲያንን ትንሽ ለማጠናከር ሄደን ጥቂት ቃላት እንናገራለን" አለ። መ-...

10 መናገር ከምፈልጋቸው የመጀመሪያ ነገሮች አንዱ። ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደተመለስኩ፡ መናገር የምፈልጋቸውን፡ አንዳንድ ነገሮች፡ እዚህ ወረቀት ላይ ጽፌአለሁ። እዚህ ከጻፍኳቸው ነገሮች አንደኛው እኛ በሌለንበት ወቅት የደጉ ወንድማችን ቴይለር ህይወት ማለፍ ነው።

11 ወንድም ቴይለር ማለት ለብዙ ዓመታት በዚህ ቤተ ክርስቲያን የኖረ ሰው ነው። እርግጠኛ ነኝ፡ ሁላችንም እናውቀዋለን። እንግዶች የሆናችሁ ካላችሁ ግን፡ እናንተ ቁጭ እንድትሉ፡ ሁልጊዜ ወንበር የሚያቀርብላችሁ ያ ውድ ሽማግሌ እሱ ነው። ወንድም ቴይለርን፡ ለመጨረሻ ጊዜ ባየሁት ጊዜ፡ ወጣት መሰሎ እኪታየኝ አየሁት፡ ከሶስት ወይም ከአራት እሁዶች በፊት በሩ ላይ ቆሞ ነበር። እንዲህ አለኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ አንዳንድ በራሪ ጽሑፎችን ማግኘት እፈልጋለሁ። እነዚህን መጻሕፍቶችን ማስራጨት እፈልጋለሁ። እኛም፡ እ...

12 አንድ የተረዳሁት ነገር፡ የሰኳር ህመም ነበረበት እና ኮማ ውስጥ ገባ፡ የሰኳር ህመም እንዳለበት አያ... አያውቅም ነበር። በ—በዚያም... ሞተ። በፍጹም አልሞተም። ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለመሆን ሄደ።

13 እሱም ሁሌም ለሌሎች ሰዎች የሚያስብ፡ ታማኝ፡ እና ድንቅ ወንድም ነበር። የእርሱ ደስታ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ፡ የሚቀመጡበትን ቦታ ማዘጋጀት መቻሉ ነበር። ታውቃላችሁ፡ ምናልባት፡ አድማሱን ሰንሻገር፡ ወንድም ቴይለርን እዚያው ማየት መቻላችን፡ በዚያም ማደ፡ የምንቀመጥበትን ቦታ በማፈላለግ ተጠምዶ ስናየው ደስ አይልምን?

14 በወንድም ቴይለር መታሰቢያ፡ ይመስለኛል... በቀብር ሥነ ስርዓቱ ላይ ለመናገር ከወንድም ኔቪል ጋር አልተገኘሁም፡ ነገር ግን፡ ለመበለቲቱ፡ የምስጋና ቃል መናገር እፈልጋለሁ። ይመስለኛል፡ እህት ቴይለር፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ በሆነ ቦታ አለች፡ ቅን ልቧን እግዚአብሔር ይባርከው!

15 ወንድም ቴይለር፡ አንድ ቀን እንዲህ አለኝ፡ "ወደዚህ ናና ጠይቀኝ። አንተ መጥተህ አሳ ታጠምድበት ዘንድ፡ አነስተኛ ኩሬ ቆፍሬአለሁ፡ በውስጡም አሳዎች ጨምሬበታለሁና መጥተህ እየኝ።" እሱ ሁሌም ስለሌሎች ያስባል። መዳንን ይስጠው ዘንድ፡ ስለእርሱ ሁሌም የሚያስበለት ስለነበረው ነው፡ እርሱም ክርስቶስ ነው።

16 እኔ እንደማሰበው፡ ለመታሰቢያው ያህል፡ ዛሬ ጠዋት ቤተ ክርስቲያናችን አንድ አካል ሆነን ተሰብሰበን ሳለን፡ ሁላችንም በአንድነት ተነስተን፡ አንገታችንን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ እናድርግ።

17 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ እኛ ዛሬ ጠዋት እንደ ሰዎች፡ በዚህ የ— የአምልኮ ሰፍራ ከተገኘን መካከል... ታላቁ ክንድህ በመካከላችን ተንቀሳቅሶ ከምንወዳቸው ውድ ወንድሞቻችን አንዱን ወሰደ፡ እርሱንም አንተ እንደወደድከው እናውቃለን። ጌታ ሆይ፡ ለዚህ ሁሉ የራስህ ምክንያት አለህ፡ አለበለዚያ እንዲህ አይሆንም ነበር፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳችን፡ “እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ ይደረጋል፡” ይላልና። ይህም አድርጓል።

18 ወደዚህ ዓለም፡ ሰንመለከትም፡ ወንድማችንን መቃብር ሊይዘው እንደማይችል፡ ተፈጥሮ በሁሉም መንገድ ሲነግረን እናያለን፡ እርሱ በምድር ያደርገው ዘንድ ወደዚህ የላክኸውን ዓላማ ፈጽሟልና። በጎና፡ ቅን ወንድም ነበርና።

19 ይህንንም በእጽዋት የሕይወት ዑደት ውስጥ፡ እና ብርሃንን ሊሰጠን በማለዳ በምትወጣ የፀሐይ የሕይወት ዑደት ውስጥ እናየዋለን። ጸሐይዋ በእኩለ ቀን መካከለኛ ዕድሜ እንዳለው ትሆናለች። የእግዚአብሔር ዓላማ ፈጻሚ ስለሆነች፡ አዲስ እና ፍሬሽ በመሆን፡ እንደገና በጥዋቱ ለመነሣት፡ በመሸ ጊዜም እንደገና ትሞታለች።

20 አበቦች ሲያብቡ እና ምድርን ሲያስውቡ የቀብር ቤቶችን፡ የሰርግ ቦታዎችን ሲያጌጡ፡ እና ዓላማውን ሲፈጽሙ እናያለን፥ ልቧን ከፍታ፡ ንቦችም፡ በነጻ ማር ትሰጣቸዋለች፡ ለቀማሚው መዓዛን፡ ለሚፈልጉትም ውበት ትሰጣቸዋለች። ያላትን ሁሉ፡ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ታደርጋለች፡ ከዚያም ጭንቅላቷን ጎንበስ ታደርጋለች። የጸደይ ወቅት ሲመጣ ግን፡ እንደገና ትበቅላለች፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ዓላማ ፈጻሚ ናት።

21 ስለዚህ በተፈጥሮ ሁሉ፡ እና በመጽሐፍ ቅዱስ፣ እና በተሰፋው ቃል፡ እና በመንፈስ ቅዱስ ሁሉ ፊት፡ ወንድማችን ቴይለርም፡ የእግዚአብሔርን አላማ እንደፈፀመ በማወቅ፡ እኛም፡ በልባችን ደሰ ይለናል። እሱ አይነሣም ማለት ካልን መጽሐፍ ቅዱሳችንን፡ አምላካችንን፡ እንዲሁም ትንሣኤ እንዳለ እናውቅ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠንን ሁሉ፡ መካድ እንደ ማለት ነው። ስለዚህ እርሱን ዳግመኛ የምናይበትን ጊዜ እንናፍቃለን፡ ወጣት እና ጤናማ የሚሆንበት የማይታመምበት ወይም የማያረጅበትን ጊዜ እንጠባበቃለን።

22 ውድ ሚስቱን፡ ታማኟ ባልንጀራውን ባርካት። ጌታ ሆይ፡ አብረው ወደ ኩሬው ሲሄዱ፡ እና በአግዳሚው ወንበሮች ላይ፡ በዚያ ተቀምጠው፡ እያወሩ፡ አሳ ሲያጠምዱ፡ ፍቅራቸው ምን ያህል ድንቅ እንደነበረ፡ እስክናያቸው ድረስ፡ እጅግ እንናፍቃቸዋለን።

23 አሁንም የእምነት አርበኞች የድል ቀሰታቸውን ወድረው፡ የሚሰለፉበት ታላቁ ቀን እንደሚመጣ እናውቃለን፡ መላእክቶችም... በዝማሬዎቻቸው አየሩን የሚሞሉበት ቀን ይሆናል። በዚያም እንደገና እናያቸዋለን።

24 እስከዚያ ድረስ፡ ጌታ ሆይ፡ አይዞ በለን። ባርከን እርዳንም። ወንድም ቴይለርን፡ እኛ እና ወደዚህ ቸርች የሚመጡት ሁላችንም፡ እርሱ በር ላይ

ቆሞ የእግዚአብሔር ቃል ለመስማት የሚመጡትን፡ እንዲቀመጡ እንዲያርፉ እንዲሁም ዘና እንዲሉ ስፍራን ሲፈልግ ይናፍቀናል።

25 በቀደምለት እርሱ ያረፈለታ፡ ጌታ ሆይ፡ ይቀመጥ ዘንድ ታላቁ የእግዚአብሔር የመላእክት አለቃ በዚያ በበሩ አጠገብ እንዲቆም፡ ጌታ ሆይ፡ ስፍራም፡ ታዘጋጅለት ዘንድ፡ ይቀመጥ ዘንድ ጸለይሁ። ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ፡ "መሐሪዎች ምሕረትን ያገኛሉ" ተብሎ ተጽፏል። እነሆ ዳግመኛ እስክናየው ድረስ፡ ጌታ ሆይ፡ በሌላኛው ምድርም፡ እስክንገናኝ ድረስ ትዝታዎቹን በልባችን አቆይልን። የምንለምንህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። ኣሜን።

26 በእንግዶች፡ እና ለአምልኮ ወደ ቤተክርስቲያናችን፡ ወይም ወደዚህ ሕንጻ በሚመጡ ሁሉ፡ ለረጅም ጊዜ፡ እየታሰበ ይኖራል። እስከዚያ ቀን ድረስ፡ ነፍሱ በእግዚአብሔር ፊት በሰላም ትረፍ።

27 እኛም፡ አንድ ቀን፡ ተራ በተራ፡ ስፍራውን ለቀን፡ አንድ በአንድ እንሄዳለን። እንግዲህ፡ ጊዜ እያለን፡ እና ማድረግ ስንችል፡ ለሚመጣው ጊዜ ራሳችንን እናዘጋጅ፥ መቼ እንደሚመጣ አናውቅምና። ቀጥሎ ማን እንደሚሆን አናውቅም። እንግዲያውስ፡ ምናልባት ቢመጣ፡ ተረኛ ከሆንን፡ ዘወትር የተዘጋጁ እንሁን።

28 አሁን፡ ማስታወቂያዎችን መናገር እፈልጋለሁ። ስለዚህ፡ በቅርቡ፡ እንደሚመስለኝ፡ ምናልባት፡ ከተመለስኩበት ጊዜ ጀምሮ ከባለአደራዎቹ ጋር አልተነጋገርኩም፡ ስ—ስለ ቤተ ክርስቲያን ግንባታ ሂደት፡ ወይም ቤተ ክርስቲያናችንን ለማዘጋጀት፡ በቀጣይነት ማድረግ ያለብን አልተነጋገርንበትም። በመቀጠል፡ ይቅርታ አድርጉልኝ፡ በ—በሰባት ማሕተሞች እቀጥላለሁ፡ ከዚያም በሰባቱ ጽዋዎች፡ እና ወዲያውኑ ልንገባባቸው የሚገቡን፡ ብዙ ነገሮች እንዳሰሳለን።

29 አሁንም፡ በሚቀጥለው እሁድ ጥዋት፡ በዚያ፡ በኤልዛቤት ታውን፡ ኬንታኪ እገኛለሁ፡ በወንድም ኤል.ጂ. ሁቨር ዘንድ፡ የ—የምርቃት ስነ ስርዓት አለ። ያም ተበርናክሉን፡ በኤልዛቤትታው በኬንታኪ የገዙትን አዲስ ተበርናክል ለማስመረቅ ነው። በኤሊዛቤት ታውን መስመር እስከ 62 ተከትሎ፡ ወይም፡ በ 31፡ ማዞርያ ድረስ፡ ማለቴ ነው። ልክ በመታጠፊያው ላይ፡ ወደ ኤልዛቤት ታውን ይወስዳችኋል። የአንድ ሰዓት ያህል ነው። ወደ ሠላሳ-አምስት፡ ወይም አርባ ማይል ይርቃል። ይመስለኛል፡ ወደ አርባ ማይል ያህል፡ በነገራችን ላይ... በ 31፡ ሠላሳ-አምስት ማይል፡ ገደማ ይርቃል፡ በሌላ መንገድ፡ በማዞርያው በኩል። በመልቤሪ ጎዳና ላይ ነው።

30 የምርቃት ሥነ ስርዓት። ወንድም ሁቨር እንደተለመደው በአሥር ሰዓት ላይ የሰንበት ትምህርት ያስተምራል። በቀጣይ እሁድ፡ ሕዳር አስራ አንድ፡ ከአስራ አንድ እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ድረስ፡ የምርቃት ሥነ ስርዓቱ ላይ እኔ እሰብካለሁ።

31 በማስታወቂያ ስሌዳው፡ እዛ ላይ—የዜናው ዝርዝር ተለጥፏል። በዚያም... የመንገዱን አድራሻ ከዚያ ማግኘት ትችላላችሁ። በመልቤሪ ጎዳና ላይ ነው። ወይም አቅጣጫውን እ—እነሱ ይጠቁሟችኋል... በቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ባለው የማስታወቂያ ስሌዳ ላይ ይገኛል።

32 ከዚያም፡ በ—በኅዳር ሃያ-ሁለት፡ በ—በሽሪፖርት፣ ሉዊዚያና እ—እገኛለሁ፡ በሀያ-ሁለት፡ ሀያ-ሦስት፡ ሀያ-አራት፡ ሀያ-አምስት፡ እና—እና በሃያ-ስድስት። አምስት ቀን፡ ይመስለኛል፡ በሽሪፖርት፡ ሉዊዚያና፡ ላይፍ ተበርናክል ላይ እገኛለሁ። በወንድም ሙር ዘንድ ነው። የወርቅ ኢዮቤልዩአቸውን እያከበሩ ነው። የጴንጤቆስጤው ጉብኝት ከሃምሳ አመት በፊት በሽሬቬፖርት፣ ሉዊዚያና፣ ውስጥ ወረደ፡ በዚህ ወር በሃያ-ሁለት ላይ ነው። የዛሬ ሐምሳ አመት፡ የመጀመሪያውን የጴንጤቆስጤ መልእክት ተሰበከ። በዚያም፡ በሉዊዚያና፡ መንፈስ ቅዱስ ወረደ። ለዚያም መታሰቢያ ያደርጋሉ፡ እናም ይህ የወርቅ ኢዮቤልዩ ነው። በሽሪፖርት፣ ሉዊዚያና፡ በላይፍ ተበርናክል፡ ከወንድም ሙር ዘንድ፡ ስለ ኢዮቤልዩ፡ አምስት ምሽቶች እሰብካለሁ።

33 በአካባቢው ወዳጆች ካሏችሁ፡ እና፡ ልትጽፉላቸው የምትፈልጉ ከሆናችሁ፡ ሌላም ቢሆን፡ ቢመጡ ደስ ይለናል። በቅርብ ስለሚደረጉ ስብሰባዎች ንገሯቸው።

34 ስለ ላይፍ ተበርናክል በተመለከተ፡ ምናልባት ከእናንተ መካከል ወንድም ሞር ጋር የነበረ ካለ፡ ድንቅ ወንድም ነው። የዕድሜ ባለጸጋ የደቡብ ሰዎች፡ ድንቅ ሰዎች ናቸው። እነሱን በቀላሉ ማሸነፍ አትችሉም። ስለዚህ፡ በላይፍ ተበርናክል፡ በሽሪፖርት ዙርያ የሚኖር ማንም ሰው ቦታውን ሊነግራችሁ ይችላል። በሽሪፖርት ወደ ሁለት መቶ ሺህ ሰዎች ገደማ ናቸው። እና ጥሩ ከተማ፡ እና ብዙ እንግዳ ማረፊያዎች ያሉባት ናት። ስለዚህ...

35 ተበርናክሉም እጅግ ግዙፍ፡ በጣም ግዙፍ ተበርናክል ነው። በተጨማሪም ወለሎች፣ በረንዳዎች፣ ዋና ክፍል፣ እና ሌላ ክፍሎች አሉት። እጅግ ብዙ ክፍል አለው። አምስት ሺህ ሰዎችን ማስተናገድ የሚችል ከማዘጋጃ ቤት ፊት ለፊት ነው። ወደ ማዘጋጃ ቤት ለመሄድ፡ እዚህ መንገዱን እንደ—ማቋረጥ ነው።

36 ሬቨረንድ ጃክ ቲ. ሙር፡ ወ—ወይም በሽሪፖርት፡ ሉዊዚያና የሚገኝ ላይፍ ተበርናክል። በሃያ-ሁለት ይጀምራል። ከእሮብ-... ሐሙስ እስከ እሁድ ይቆያል። ይቅርታ። ሐሙስ፣ አርብ፣ ቅዳሜ፣ እሁድ፣ አምስት ቀናት ሳይሆን፡ አራት ቀናት። ያም ሀያ-ሁለት፣ ሀያ-ሶስት፣ ሀያ-አራት፣ ሀያ-አምስት ይሆናል። የ—የሕዳር እቅድ ነው፡ ብዬ እሰባለሁ።

37 ሌላው ደግሞ፡ ይህ እኛ ያለንበትን፣ እዚህ ካለው ቤተ ክርስቲያናችን ጋር በተያያዘ፣ የቤተክርስቲያኑ ግንባታ ፕሮጀክት ሂደት ያለበትን ሁኔታ እንመለከታለን። ሥራ ተቋራጮቹ በቂ ሠራተኞችን በማሰባሰብ፡ ኢያችሁ፡ በአሥር ቀናት ውስጥ፡ በፍጥነት እንገባበታለን ብለው ነግረውናል። የሚጠብቁት ከከተማው ይሁንታ ብቻ ነው። ታውቃላችሁ፣ በጣም ብዙ የመኪና ማቆሚያ ይኖረናል፡ **ይሄኛውም** እጅግ ብዙ ይኖረናል። እናም፡ ወይ፡ ጉድ፡ ማንኛውንም ነገር መገንባት ከመጀመርዎ በፊት፡ አስተዳደራዊ ችግሮች ውስጥ ታልፋላችሁ። ወደ ሚሲዮኑ መስክ ከመመለሴ በፊት ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለስ እፈልጋለሁ።

38 ከወደ ታንጋኒካ፣ ዩጋንዳ፣ እና በዙርያው እንድሄድ ግብዣ ቀርቦልኛል። ዮሴፍ እነዚህ ተከታታይ ስብሰባዎች በየካቲት ወር እንዲጀመሩ አዘጋጅቷል።

39 ትናንት፡ ሰደርስ፡ አንዳንድ ወንድሞች፣ እነ እህት ቶምስ፣ እና ከመስክ የተመለሱ፡ ሌሎችም ነበሩ። እና እዚያም... ቤቴ ላይ ማስታወሻ አገኘሁ፡ ወ—

ወይም ከ—ደቡብ አፍሪካ ከሚገኝ ማህበር የመጣ አንድ ግብዣ አገኘሁ። ስለዚህ ምን ማድረግ እንደምንችል ለማየት፡ እየጸፍሁላቸው እገኛለሁ። ምናልባት፡ ምናልባትም፡ በየካቲት መጨረሻ ወይም በመጋቢት መጀመሪያ አካባቢ፣ በዚያን ጊዜ አካባቢ፡ ርቄ ከሄድኩ፡ ወደ ደቡብ አፍሪካ ብቅ ማለት እችላለሁ።

40 ከተቻለ ወደ ቤተ ክርስትያን ዘመናት እንድገባ፡ ክረምቱ ከመግባቱ በፊት፡ ቤተክርስቲያኒቱ ትዘጋጃለች ብዬ፡ ተ—ተስፋ አደርጋለሁ። አለበለዚያ፡ እኔ ከዚያ ስመለስ ይሆናል፡ ጌታ ኢየሱስ ቢዘገይ።

41 ትናንትና አንድ ነገር እያደረግኩ ነበር፡ ከትናንት ወዲያ ይመስለኛል፡ ቴፕ እያዳመጥኩ ነበር። ዛሬ ጠዋት እዚህ ሲያጫውቱት የሰማሁት ይመስለኛል። ከደቡብ የመጣ አንድ ወጣት ወንድም ነበር... እና እናቱ ወደ ስብሰባው መጣች። በአንደኛው ጡቷ ላይ አደገኛ ዕጢ ነበራት፣ እናም ሞት አጥሎባት ነበር። በቅርቡ በሳውዝ ፓይን፡ ከተደረጉት ስብሰባዎች በአንዱ፡ ወይም ሌላ ቦታ፡ ይመስለኛል፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ማን እንደነበረች፡ እና ከየት እንደመጣች፡ ስለነበረባት ነቀርሳ፡ ነግሯታል። እና ከእምነት ወደ ኋላ የተመለሰ ወንድ ልጅ እንዳላት፡ እርሱም አደጋ ሊያጋጥመው እንደሆነ፡ በነፍስ ግድያ እንደሚፈረድበት ነገራት። ሌላም ብዙ ተመሳሳይ ነገሮች። እናም ልጁ....

42 ይህ ሁሉ የሆነው እንዲሁ ሆነ። አደገኛው ካንሰር፡ ወይም፡ አደገኛው የነቀርሳው ዕድገት፡ ትቷታል። ይህ፡ አደገኛው ዕጢ ነቀርሳ ነው፡ ታውቃላችሁ። ከዚያ በኋላ—ለቀቃት። ብላቴናውም መንፈስ ቅዱስ እንዳለው፡ ነፍስ በማጥፋት ለፍርድ ቀረበ። እንደገናም፡ ወደ ክርስቶስ ተመልሷል። እርሱም በቴፕ መልክ አዘጋጅቶት፡ ሲያጫውቱት—ሰማሁ። ደስ የሚለውን፡ የደቡብ ዘዬ ስምታችሁታል? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—እርታዒ።] ሲናገር፡ "እዚህ በሰሜን ካሮላይ'ነር ውስጥ፡" አለ። ኦህ፡ እነዚህ የደቡብ ህዝቦች፡ እንዴት እንደምወዳቸው። እርሱንም... እግዚአብሔር ባረከው። እርሱም፡ "ወንድም ብራንሃም፥ ለጉባኤያችሁ ሰዎች ብቻ እንጂ፡ ለሌሎች ዶክትሪን አልሰብክም እንደምትል አውቃለሁ።" "እኛ የጉባኤያችሁ አካል ነን፡" አለኝ። ስለዚህ ይህን ማለቱ፡ በጣም ደስ ይላል።

43 ሌላ ደግሞ አንድ ስዕል አለ፡ ምናልባትም፡ ዛሬ ጠዋት በማስታወቂያ ስሌዳው ላይ የለጠፉት፡ ይመስለኛል። እዚያ ከሌለ፡ ቢሊ ይለጥፈዋል። ብዙ ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ማውራት ስጀምር፡ ሰዎች አንድ ነገር ሲናገሩ፡ እሰማቸዋለሁ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ያ ብርሃን፡ ብርሃን አይቻለሁ ብለህ፡ በምናብህ አስበህ ነው።" ምናልባት፡ አሁን የቀሩ ጥቂት...

44 ምናልባት ፎቶዎቹ ከመነሣታቸው በፊት፡ ከድሮ-ሰዎች መካከል፡ ይህን ማስታወስ የሚችሉ ጥቂት የቀሩ ግለሰቦች አሉ። ከረጅም ጊዜ በፊት፡ ስለዚህ ጉዳይ ስናገር ሰምቶኝ የሚያውቅ ሰው አለ? ተመልከቱ። አራት ወይም አምስት እጆች። እዚህ ጋር እህት ስፔንሰር አለች፡ ወንድም እና እህት ስላውተር፡ ሌ—ሌላም አንድ ወንድማችን **እዚህ** ጋር፡ ሌላ ወንድማችንም **እዚያ** ጋር አለ። ከድሮዎቹ-ሰዎች መካከል የቀሩት አምስት ወይም ስድስት ሰዎች አሉ።

45 እንግዲህ፡ አሁን፡ ከጊዜ በኋላ፡ የካሜራው ሜካኒካላዊ አይን ምስሉን አነሣው። ከዚያም ወደ ዋሺንግተን፡ ዲሲ ተወሰደ፡ በመርማሪ ባለሞያዎች አልፎ

ተመልሶ መጣ፡ “የተነካካ ወይም ሌላ ነገር የለውም።” “ሌንሱን የነካው ያ ብርሃን ራሱ ነው፡” አለ። ይህን ያለው ጆርጅ ጄ. ላሲ ነው። በዚያም ሰሙ ፈርሞበታል። አያችሁ?

46 እንግዲህ፡ ብዙ ጊዜ፡ አይቼ ሰናገር፡ ትሰማላችሁ፡ “**በዚህ** ሰው ላይ ጥቁር ጥላ አጥሎበታ። የሞት ጥላ ነው።” ይህን ሰናገር ሰንቶች ሰምታችሁኝ ታውቃላችሁ? ብዙ ጊዜ፡ አያችሁ፡ ብዙ ጊዜ። እንግዲህ፡ ካሜራው ያንን አንሥቶታል። እዚህ ከእኛ ጋር አለ።

47 አንዲት ሴት ወደ አንዲት እህት መጥታ፡ በሳውዝ ፓይን ሰለነበረን፡ በካሮላይና ባደረግነው ሰ—ሰብሰባ ላይ የነበረውን ድንቅ ነገር አጫወተቻት። በዚህ ሁኔታ፡ ሴትየዋ በሁለቱም ጡቶቿ ላይ በወጣው ካንሰር ሞት አፋፍ ላይ ናት። ሐኪሞቹም ተሰፋ ቆርጠውባት ለሞት ሰጥተዋታል። ሴትየዋም ማንነቷንና፡ ከየት እንደመጣች እየነገርኳት ሳለሁ፡ ጎንበሰ ብላ ፎቶ አነሳቻት። “በላይሽ ላይ ጥቁር ጥላ አጥሎብሻል። በሞጥ ጥላ ውሰጥ ነሽ፡” አልኳት። እና ሴትየዋ ፎቶዋን አነሳች። የካሜራው ሜካኒካል አይን፡ የሞት ጥላውን አነሣው።

48 **አሰርቱ ትእዛዛት** የሚለውን ፊልም ካያችሁት፡ እና የሞት መልአክ፡ ሲመላለሰ ካያችሁት፡ ያ ጥቁር፡ ጨለምለም-ያለውን ጥላ፡ ምሰሉ ላይ ወጥቷል። እና አሁን በማሰታወቂያ ሰሌዳው ላይ የተለጠፈ ይመሰለኛል። ካልሆነ ግን፡ ቢሊ ሰምቶኛል፡ ሰለዚህ፡ በማሰታወቂያ ሰሌዳው ላይ ይለጥፈው። በዚያም ወደ ግለሰቧ የሚጠቁም ቀሰት አለ። ግለሰቧም፡ ጥላው ከሴቲቱ ተነሣላት፡ በተአምር ተፈወሰች። ብቻ ግን ልክ እንደ ኮፍያ የመሰለ ነገር፡ እንደ ጥቁር ጭሰ በሴትዬዋ በራሷ ላይ በዙርያዋ አለ፡ በዚያ በካንሰሩ ላይ እንዲህ ተንጠልጥሎ፡ ከዚያ ወጣ። እርግጥ ነው፡ ይህ ነገር ከካንሰሩ የተነሣ፡ ወደዚያ፡ ወደ ጥላው የሚፈሰሰ፡ ሞት ነው።

49 መቼም፡ ለሰዎች እውነቱን ለመናገር የቱንም ያህል ብትሞክር፡ እውነት አይደለም ብሎ የሚጠራጠር ሰው ይኖራል። እና ሁል ጊዜ እውነትን የምትናገር ከሆነ፡ ልክ እንደ—እንደሆንክ ታውቃለህ።

50 በ—በምዕራብ ላይ አንድ ጓደኛ አለኝ፡ አርብቶ አደር ነው። እና—እና የአካባቢ ጥበቃው የበረዶ መኪና ለመግዛት ወደ አራት ሺህ ዶላር አውጥቷል፡ ይህም በአሰቸጋሪው ወንዝ ሸለቆ ውሰጥ የቀረውን የኤልክ መንጋ ለመቁጠር ነው። ዛሬ ቤተ ክርሰቲያን ውሰጥ ቁጭ ብሎ ያለው ሚሰተር ጄቨርዝ፡ ወደ ክርሰቶሰ ያመጣሁት እኔ ነኝ፡ ፍጹም የማያምን ነበር። አብረን በፈረሰ ግልቢያ የሄድንበትን ጊዜ ሰናገር ሰምታችኋል። እና ከዳርዊን ሰነ ሐሳብ በቀር ሌላ ነገር አያምንም ነበር። “ይህ ከድንግል-የተወለደ፡ ሕፃን፡ ለእሱ ከንቱነት ነበር።” በቀደም ምሽት እሱ ክርሰቶሰን በተቀበለባት ቦታ ላይ ካምፓችንን ተከልን።

51 እናም ይህ ሰው ነገራቸው። “አሁን፡ ያንን መኪና፡ ያንን የበረዶ ተሽከርካሪ መግዛት አያሰፈልግም፡” አለ። “ምን ያህል ኤልክ መኖራቸውን እኔ በትክክል እነግራችኋለሁ፡” አላቸው። “አሰራ ዘጠኝ ናቸው፡” አለ። “ሃያ ነበሩ-... ሃያ-አንድ ነበሩ፡ ሁለቱን ገድያለሁ፡” አልው። ይህን የሚነግረው ለደን ጥበቃ ሰራተኛው ነው። ከአንድ በላይ መግደል የማይታሰብ ነው። ሰለዚህም እንዲህ

አለ፡ “ሃያ-አንድ ነበሩ፡ ከመካከላቸው ሁለቱን ገድያለሁ። አሥራ ዘጠኝ ይቀራሉ።”

እርሱም፡ “አዎን፡ ጄፍ፡ ሁለቱን እንደገደልክ አውቃለሁ።”

እሱም “እኔ ገድያለሁ፡” አለው።

52 በኋላም፡ የበረደው መኪና ይዘው፡ ወደዚያ ወጡ፡ አስራ ዘጠኝ ኤልኮችን አገኙ። እሱም “ይኸውልህ ቢሊ፡ ለሰው እውነት ብቻ ተናገረው፡ አያምንህም፡” አለኝ።

53 ስለዚህ ነገሮች እንዲህ ናቸው። ለሰዎች እውነቱን መናገር ትችላለህ፡ ቢሆንም እነሱ ግን... በጣም በብዙ አለመግባባት እ—እና ስለ ነገሮች በብዙ መዋሸት ስለኖሩ እውነትን ስትነግራቸው እውነትን ነው የምትናገረው ብለው እስካያምኑ ድረስ ሆነዋል። አያችሁ?

54 እኛ ግን ያንን እውነት በማረጋገጫ የሚያረጋግጥ የሰማይ አባት ስላለን በጣም እናመሰግናለን። እውነት ነው። እንግዲህ ይህች በምድር ላይ የመጨረሻዬ ቀን ከሆነች፡ ስለ... ስለእነዚህ ነገሮች እውነቱን እንደተናገርኩኝ ሳይንሳዊ ምርምር እና ማረጋገጫዎች ሳይቀር አረጋግጠውታል። በትክክል። እውነት ነው። ስለዚህ ምናልባት በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ ሊሆን ይችላል። ቢሊ፡ ክፍል ውስጥ ነህ? ምስሉን፡ በእጅህ ይዘኸዋል? ይዘኸው ከሆነ፡ እንግዲያውስ፡ ወደዚህ አምጣውና፡ ሁሉም እንዲያዩት፡ እዚህ ጋር ትሰቅለዋለህ። እንጃ ብቻ፡ እኔ አላውቅም። ሰሌዳው ላይ—ብርሃን መኖር አለበት።

55 ምስሉ ይሄኛው ነው—እዚህ ጋር አለ። የሚታያችሁ አይመስለኝም። ቢሆንም **እዚህ** ጋር በሴትየዋ ራስ ላይ የከበባት የሞት ጥላ ማየት ትችላላችሁ። ይህች ሴት ይህን ፎቶ ያነሳችበት፡ በእውነቱ ይታይ እንደሆነ ለማሳየት፡ ከሱ ጋር የሚሄድ አባሪ-ጽሑፍ **እዚህ** አለ። እናም ይኸው፡ በ—በዚያ አለ። የከበባት የሞጥ ጥላ ነው።

56 እዚያ ጋር፡ ሴቲቱ ትታይሃለች? ወንድም ኔቪል፡ ያየሃት፡ ይመስለኛል፡ አይደል? [ወንድም ኔቪል “አዎን፡” አለ።—አርታዒ።] ኧሃ-ሃህ።

57 ስለዚህ፡ ቢሊ ምናልባት በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ ያስቀምጠዋል፡ ከቻልክ፡ ቢሊ። ናና፡ ወስደህ፡ ወደፊት አስጠጋውና ሰሌዳው ላይ ሰቀለው፡ ሰዎች ሲወጡ ሁሉም ያዩታል። እሱ ወይም ዶክ፡ አንዳችሁ። አሁን ሳስበው፡ ምናልባት፡ እስኪታያችሁ ድረስ እጅግ ግልጽ ነው፡ ቢሆንም ይህ አይነቱ ምስል ብዙ ጨለማ አለው። ለማንኛውም ወደዚያ ያመጣዋል፡ ስትወጡ፡ ሁላችሁም ታዩታላችሁ።

እንግዲህ፡ ማስታወቂያዎቹ ሁሉ እንዳትረሱ።

58 አሁንም፡ ዛሬ ጥዋት፡ ቤተክርስቲያኒቱን ያበረታል ብዬ ያሰብኩትን ጥቂት ነገር እናገራለሁ፡ የበለጠ ነገር ሊሰጣችሁ የሚችል ነገር ነው...

59 [ወንድም ዶክ ብራንሃም “አምፖሉን ትፈልገዋለህ?” አለ፡—አርታዒ] ምን አልከኝ? [አምፖል አጠገብህ እንዲሆን ትፈልጋለህ?”] አዎን፡ ዶክ፡ ከቻልክ። ጥሩ ይመስለኛል።

60 ይህንን መጠቀም እፈልጋለሁ። እ... ባለፈው ሳምንት፡ሰላልበሩ፡ ዛሬ የተሻለ ይሆናል ብለን እናስባለን። ስለዚህ ጉዳይ መናገር ፈልጌ ነበር፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ከ—ከአንዲት እህት ህልም ጋር የተያያዘ ነው።

61 ዛሬ ጠዋት እህት ሼፐርድ ቤተክርስትያን ውስጥ አለች ይሆን። በቀደም ምሽት አገኘኋት። እና ይህችን ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ ባየኋት ጊዜ፡ በእውነቱ፡ ማን እንደሆነች እንኳን አላውቅም ነበር። እዚህ ናት? አይመስለኝም። አለች። ቅር አይልሽም አይደል፡ እህት ሼፐርድ፡ ስለ ህልሙ ብናገር፡ ምናልባት ቅር የሚያሰኝሽ ነገር አለው ይሆን? ቅር አይልሽም፡ አይደል? በጣም ጥሩ። በጣም ጥሩ ነው።

ወደዚያ ከማለፋችን በፊት፡ አሁንም ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

62 ቸር የሰማይ አባት ሆይ፡ ስለ ቸርነትህ እና ምህረትህ ሁሉ እናመሰግንሃለን። አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ በራእይ ወደ እኛ እንደሚመጣ፡ በመንፈስ ቅዱስ እንደተረጋገጠ፡ እና በመፅሃፍ ቅዱስ እንደተደገፈ፡ የሕያው እግዚአብሔር ቃል እናጠና ዘንድ አሳረፍን። በዙሪያችን ያሉ የክፋት ሃይሎችን እያየን ነውና፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ምን ማድረግ እንዳለብን እናውቅ ዘንድ ማስተዋልን እንድትሰጠን እንጸልያለን። ያ ጦርነት፡ የመጨረሻው ጦርነት ሊደረግ ነው። ጌታ ሆይ፡ እርዳን። እንደ እውነተኛ፡ ጠንካራ ተዋጊዎች፡ የእምነትን ጋሻ አንስተን፡ ሰይፍ በሆነው፡ በእግዚአብሔር ቃል፡ ወደፊት እንቀጥል ዘንድ እርዳን። በኢየሱስ ስም። ኣሜን።

63 አሁን፡ ወደፊት መቀጠልን ሰናስብ፡ ውጊያው፡ ልክ ለሰልፍ እንደ ተዘጋጀ ው—ውጊያ፡ የእምነትን ጦርነት ለመዋጋት፡ ወደ ተግባር ለመግባት፡ ት—ትክክለኛው ውጊያ መዋጋት እናሰባለን።

64 እዚህ እህት ሼፐርድ፡ እና ወንድም ሼፐርድ፡ ወደዚህ ተበርናክል ከሚመጡት፡ በጣም ጥሩ ወዳጆቻችን ናቸው። የተወደዱ የእግዚአብሔር ልጆችም ናቸው። እ—እና እህት ሼፐርድ፡ የተላኩልኝ ፖስታዎች ሳነሳ፡ አንዳንድ ቢሊ መልሰ የሚሰጥባቸው አሉ፡ ለምሳሌ አንድ ሰው፡ “ብዙ የጸሎት ጨርቆችን ላኩልን” ሊል ይችላል። እኔ እጸልይባቸዋለሁ። እሱ ይመልሳቸዋል። የግለሰብ ደብዳቤ ሲሆን ግን፡ እኔ ራሴ መልሰ መስጠት አለብኝ፡ አያችሁ። ስለዚህ የግል ፖስታዬን አንስቼ፡ ወደ ቤት አመጣሁት። ማንበብ ጀመርኩ እና፡ “ከእህት ሼፐርድ፡” ይላል። እና ከ—ከጥቂት ወራት በፊት፡ ያየችው ህልም ነበር። እሰከ ሁለት ወይም ሶሰት እሁዶች በፊት በትክክል መረዳት አልቻለችም ነበር፡ እናም በ—**በሰባት የቤተክርሰቲያን ዘመናት** እ—እና በሁለተኛው ጴጥሮስ፡ ስለ—ሰባቱ ፍሬዎች ሳስተምር፡ ሁለተኛው ጴጥሮሰ 1 ላይ፡ ምን ማድረግ እንደሚገባን፡ “በእምነታችን ላይ መጨመር።” አያችሁ?

65 በመጀመሪያ፡ መሠረቱ፡ እምነት ነው። በሁለተኛ ደረጃ፡ በእምነታችሁ፡ በጎነትን ጨምሩ፥ በበጎነትችሁ፡ እውቀትን፥ በእውቀት፡ ራሰን መግዛትን፥ ራሰን በመግዛት፡ መጽናትን፥ በመጽናትም፡ እግዚአብሔርን መምሰል፥ እግዚአብሔርንም በመምሰል፡ የወንድማማች መዋደድን፥ የወንድማማች መዋደድን ጨምሩ፥ ከዚያም ፍቅር ነው፡ እሱም የመአዝን ድንጋይ ነው። እነዚህ ሰባት ነገሮች። ሰባት የቤተክርሰቲያን ዘመናት፡ አያችሁ፡ እና ሰባት

የቤተክርስቲያን ከዋክብት፡ እና ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ አንድ ላይ የተጣመሩ ናቸው።

66 እንግዲህ፡ የክርስቶስ አገልጋይ ለመሆን የሚያስፈልገው ያ ነው። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን፡ ሙሽራውን፡ ገለሰቧ፡ ሴቲቱን፥ ቤተክርስቲያንን በሰባት የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ሠራት። ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት ሙሽራይቱን መሰርተው ሰሯት። አንዳንዶቹ **ከዚህ** ዘመን፣ ሌሎች **ከዚያ** ዘመን፣ ሌሎችም **ከዚያ** ዘመን፣ ሁሉም በአንድነት፡ በፒራሚድ ቅርጽ ተሰራች።

67 ልክ እንደ ሄኖክ፡ ፒራሚዶችን የሰራቸው፡ እሱ እንደሆነ እናምናለን። የመደምደሚያው ድንጋይ በላያቸው አልተቀመጠባቸውም፡ ይህም የመአዝን ራስ ድንጋይ የሆነው በመጠላቱ ነው። ያንን ያቀረብነው እንደ ዶክትሪን ሳይሆን፡ ለግንዛቤ ብቻ ነው፡ ለዚህች ቤተክርስቲያን ብቻ ነው። እነዚህ...

68 እግዚአብሔር በሦስት ራሱን ፍፁም ያደርጋል። በአንዱ አምላክ ሦስት መገለጫዎች "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ፣" እራሱን ፍጹም ያደርጋል። በጸጋ ስራዎቹ ማለትም "በመጽደቅ፣ በመቀደስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፣" ፍጹም ሆነ፡ እራሱን ፍጹም ያደርጋል። በሦስት ምጽአቶች ራሱን ፍጹም ያደርጋል፥ በመጀመሪያ ጊዜ፡ ሙሽራውን ሊዋጅ፣ ሁለተኛው ጊዜ፡ ሙሽራውን ለመቀበል፣ በሦስተኛው ጊዜ፡ በሚሊኒየም ከሙሽሪት ጋር። እና ሁሉም ነገር በሦስት ውስጥ የተፈጸመ ይሆናል። ሰባት ደግሞ የእግዚአብሔር የአምልኮ ቁጥር ነው። እግዚአብሔር በሰባት ይመለካል፡ ሙሉ ይሆናል፡ አሁን ፍጹም እና ሙሉ ይሆኗል።

69 የሚገርመው ነገር፡ በዚህ ውስጥ ይህን ለማምጣት ሳይሆን፡ ይህን ላሳያችሁ ነው፡ የባለፈው የያዝኩት አጋዘን በአንዱ በኩል አምስት በሌላው በኩል ሦስት ነጥቦች ነበሩት፥ እያችሁ፡ ጸጋና ፍጽምና።

70 አሁን ይህን አስተውሉ፡ ያም ክርስቶስ። እግዚአብሔር ሦስት መጽሐፍ ቅዱሶችን ጻፈ። የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ዞዲያክ ተብሎ የሚጠራው፡ በሰማይ ነበር። አሁን፡ መጽሐፈ ኢዮብን የማታውቁት ከሆነ፡ ዝም በሉ፡ ምክንያቱ፡ ይህን ያብራራው ኢዮብ ነውና፡ ወደ ሰማይ እየና በዚያ ያሉትን ሰም ሰጣቸው።

71 እና አስተውሉ፡ ዞዲያክ፡ በምን ይጀምራል? በዞዲያክ ውስጥ የመጀመሪያው ነገር ቪርጎ ነው። በዞዲያክ ውስጥ የመጨረሻው ነገር አንበሳው ሊዮ ነው። የክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት፡ በድንግል በኩል። ሁለተኛው ምጽአቱ፡ አንበሳው ሊዮ፡ የይሁዳ ነገድ አንበሳ ነው።

72 ሄኖክ በዘመኑ፡ ወይም በዚያን ጊዜ፡ ፒራሚዱን አጠናቀቀ። እንግዲህ... እርግጥ ነው፡ ይህ እንዴት እንደነበረ ዳራውን ለማሳየት እና ፒራሚዱ በክፍል እና በሁሉም ነገር እንዴት እንደተገነባ ለማሳየት ወዘተ ጊዜ የለንም። ይህ ሰለ መጨረሻውን ዘመን አሁን በግልፅ ያሳያል። አሁን እንደ መለኪያቸው መሰረት፡ በንጉሥ ቤት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። የመደምደሚያው ድንጋይ ግን ገና በፒራሚዱ አናት ላይ ፈጽሞ አልተቀመጠም። እና ከሥነ ሕንፃ፡ ወ— ወይም ከግንበኝነት እይታ አንጻር፡ ድንጋዮቹ በትክክል ተቀምጠዋል። ሌላው ይቅር፡ ት... ትንሿ ቀጭን ምላጭ እንኳን አታልፍም... እንዴት እንደተገነባ አያውቁትም፡ አይረዱትም፡ ምርግ በተደረገበት በጎኑ በኩል ምላጭ ማለፍ

እንኳን አይችልም። ደግሞም ምርግ የለበትም። እጅግ ፍጹም ነው፡ አንድ ላይ ተጣብቀዋል።

73 ስለዚህ ክርስቶስ እና ቤተክርስቲያን አንድ ሲሆኑም ይህ ነው። በመካከላቸው ምንም ምርግ የለም። በመካከል ምንም የለም፥ እግዚአብሔር እና ሰውዬው ብቻ። እግዚአብሔር፡ ክርስቶስ፡ እና ሰውዬው ብቻ።

74 ስለዚህ፡ የመደምደሚያው ድንጋይ፡ ግን፡ በጭራሽ አላገኙትም። በኢንግላንድ ውስጥ የሚገኘውን ሰኮን የሚሉት፡ ነገስታት የሚሾሙበት ድንጋይ፡ ወይም እ—እክሊል የሚደፋበት፡ ወዘተረፈ ታውቁታላችሁ። ይሄኛው የመደምደሚያው ድንጋይ ግን...

75 የአሜሪካን ዶላር አስተውሉት። የሆነ ነገር ታያላችሁ... በአሜሪካ ዶላር፡ በአንደኛው ጥግ፡ በግራ በኩል ላይ፡ በእጆቹ ላይ ሰይፍ የያዘ... ንሰር፡ የአሜሪካው ማሕተም ይገኛል፡ በሁለተኛው በኩል፡ ይህ "የዩናይትድ ስቴትስ" ማኅተም ይባላል። በሁለተኛው በኩል ግን ፕራሚድ ይገኛል፡ በላዩም፡ ታላቁ አይን ይገኛል፡ እና ከዚህ ከሰር "ታላቁ ማሕተም፡" ይላል። ይህ ከገዛ አገራችን ማሕተም በላይ ሆኖ፡ በዚህ አገር "ታላቁ ማህተም" ለምን ተባለ? አያችሁ?

76 ምንም ነገር ብታደርጉ፡ እግዚአብሔር ያንኑ አይነት እንዲናገር ያሰደርጋል። አያችሁ? ኃጢአተኛውን ስለጉዳዩ እንዲናገር ያደርገዋል። አገሪቱ እንድትናገር ያደርጋታል። ሁሉም ስለሱ መናገር አለበት። እ—እናንተ እመኑት አትመኑትም፡ ያለ ነገር ነው።

77 አሁን፡ አስተውሉ፡ በዚያ ውስጥ አይን አለ፡ የእግዚአብሔር አይን ነው። ይህም የመአዝን ራስ የሆነው፡ የራስ ማሕተም፡ የህንጻው የመአዝን ድንጋይ፡ የፒራሚዱ የራስ ማሕተም የሆነው፡ እንዲሁም ይህ ሁሉ የሆነው፡ የእግዚአብሔር ልጅ ያልመጣው፡ ሰለተጠላ ነው። እ—አሁን፡ እ... እኔ የማልወደው ነገር አለ...

78 አንዳንድ ጊዜ እነዚህን ነገሮች በቴፕ ይቀዱና፡ በየአብያተ ክርስቲያናቱ በሌሎች ወንድሞች፡ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይደርሳሉ፡ ይህንንም ሲያደርጉ፡ ወንድሞች አንዳንድ ጊዜ የተሳሳተ ግንዛቤ ይይዛሉ፡ ይህም እኔ ሰለ ወንድሞች የማይገባ ነገር እንደተናገርኩ ያስመስሉኛል። እንደዚያ ግን አይደለሁም። እ... እንዲሁ ብትሰሙት እና ብትረዱት፡ ይኸውላችሁ፡ እኔ በማንም ወንድም ላይ አልተናገርኩም። ምክንያቱ፡ ወደ ወንድሞቻችን የምንመጣው፡ እርስ በርስ ክፉ ለመነጋገር አይደለም። እርስ በርሳችን መነጋገር ሳይሆን፡ እርስ በርሳችን መተባበር አለብን።

79 አንዳንድ ጊዜ ሰለ አንዳንድ ድርጅቶች፣ እንደ ፕሬስቢቴሪያን፣ ሜቶዲስቶች፣ እና የመሳሰሉትን ሳወራ፡ ሰዎች፡ "እነሆ፡ እሱ ያንን ይቃወማል" ይላሉ። እኔ በዚያ ባሉት ወንድሞች፡ ወይም እህቶች ላይ አልቃወምም። እኔ የማወግዘው ወንድማማቾችን የሚከፋፍለውን ሥርዓት ነው። የእግዚአብሔር ልጆች አንድ ቤተሰብ እንጂ፡ የተለያየ ቡድን እ—አይደሉም።

80 አንዳንዶቹም እንዲህ ይላሉ፡ "የፕሪስባይቴሪያን ሰለሆነ፡ ከዚያ ጋር ምንም ግንኙነት አይኖረኝም። እኔ ሜቶዲስት ነኝ።" አያችሁ? ያ፡ ልክ አይደለም። አያችሁ? ወንድማማችነትን የሚያፈርሰው የድርጅት ሰርዓት ነው። አያችሁ?

81 አሁን፡ እንግዲህ፡ ሁሌም እንደምለው፡ ባረጀ-ባፈጀ ጀልባ ወደ ወንዙ ከወረዳችሁ፡ በፏፏቴው ዙርያ የሆነ ነገር ለማድረግ ስትሞክሩ፡ እኔ ይህ እንደማይሰራ ካወቅኩት፡ እንግዲህ፡ ያን ጊዜ፡ እየጮህኩባችሁ፡ እየገጽኳችሁ አይደለም። ከጀልባው ላወጣችሁ እየሞከርኩ ነው። አያችሁ? ምክንያቱም፡ ያ ጀልባ ይሰበራልና፡ እ—እ—እናንተም በውሃው ውስጥ፡ ብቻችሁን፡ ሰጥማችሁ ትቀራላችሁ። ሰ—ስለዚህ በጀልባው ውስጥ ባለው ወንድም ሳ—ሳይሆን፡ በዚያ ወንድም ላይ የምጮኸው ከፊት ሊገጥመው የሚችለውን ነገር ለማሳየት ያክል ነው።

82 እንግዲህ፡ ሰዎች በሰኬታቸው የገነቧቸውን ሥርዓቶች ሁሉ፡ መፍረስ አለባቸው። ይኼው ነው። እንዲህ መሆን አለባቸው... በወንድማማቾች መካከል አንድነትን፡ መተሳሰብን ማምጣት አለብን። የሕይወቴ ዓላማ ያ ነው ድርጅትን ማፍረስ ሳይሆን ሰዎች ሐሳባቸውን ትተው፡ አንድ ለመሆን ጥረት ማድረግ፣ ዳግም-ከተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ ጋር ወንድማማቾች እንዲሆኑ ማድረግ ነው። አያችሁ? ይኸው፡ የኔ ሀሳብ ይህ ነው። አቋሜ ያ ነው፡ ይህም፡ እንግዲህ፡ ወንድሞች ቢያሰተውሉት ነው። እ...

83 በሙሉ ወንጌል አብያተ ክርስቲያናት ደረጃ ያሉ፡ ብዙዎች ወንድሞቻችን፣ እነ ባፕቲስትና ሜቶዲስቶች፣ ሉተራውያን እና ሌሎች ዕድል አላቸው ብለው አያምኑም። እንግዲህ፡ አሁን፡ ልክ ሊሆኑ ይችላሉ። እኔ ግን ይህን አመለካከት አልጋራም። እኔ እንደማምነው ይህ ዘመን፡ የሉተራን ዘመን፣ **ይሄኛው** ይህ ዘመን ደግሞ፡ የሰርዴስ ዘመን ተብሎ እንደሚጠራ፡ አምናለሁ። ከዚያም የፊላዴልፊያ ዘመን፡ ይህም የሜቶዲስት ዘመን ነው። ከዚያም ጴንጤቆስጤዎች፡ የሎዶቅያ ዘመን። እነዚህ ዘመናት ናቸው ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔርም፡ በእነዚህ ዘመናት ሁሉ፡ የተመረጡ ሰዎችን ወሰደ። በእዚያም፡ ዕብራውያን 11 ላይ፡ "እነርሱ ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ፡" በማለት ያሰቀምጠዋል። አያችሁ? አሁን ግን ቤተ ክርስቲያን **ከዚህ** ወጥታ፡ ወደ ጴንጤቆስጤ ዘመን እስክትደርስ ድረስ፡ በየጊዜው በታናሽ መንጋ መልክ ስትጓዝ ኖራለች።

84 እንግዲህ፣ ይህን ያልኩበት ምክንያት እህታችን በህልሟ ስላየችው ነገር ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ነው። ሕልሙም እኔ ከማስተምረው ጋር የተያያዘ ነው።

85 እንግዲህ እዚህ፡ አሁን፡ እነዚህ አንደኛ ጴጥሮስ 6ኛ እና 7ኛ ቁጥር የሚነግሯችሁ ነገሮች በሙሉ፡ በ-... በእምነታችሁ ላይ ሲል፡ ይህ ጅማሬ ነው። እንግዲህ፡ ሰዎች ዳግመኛ ሳይወለዱ እነዚህ ቁመናዎች አሉን እንደሚሉ ነግሬአችኋለሁ። በዚያም ጨዋነት የጎደለው ንግግር የተናገርኩ ይመስለኛል እንዲህ በማለት፡ "እራሱን ፒኮክ ለማስመሰል የፒኮክን ላባዎች በላዩ ላይ እንደሰካካ፡ እንደ ጥቁር ወፍ ነው።" ይህ አይሰራም። ከሱ ዘንድ የበቀሉ ተፈጥሮአዊ ላባዎች ሊኖሩት ያስፈልጋልና። የውስጠኛው ማንነቱ ያንን ላባ ማብቀል ይኖርበታል።

86 ብዙ ጊዜ ሴቶች እህቶቻችን፡ ስለ ፀጉራቸው መቁረጥ፡ እና ፊታቸው ላይ ሜካፕ ስለማድረጋቸው፡ እና ስለ አሸንክታቦቻቸው፡ እንደምከብድባቸው ሲከሱኝ ኖረዋል። ሁልጊዜም በእህቶቻችን ላይ ትከብድባቸዋለህ በማለት ሲከሱኝ ቆይተዋል። ይህ—ግን በነሱ ላይ ጥላቻ አለኝ ማለት አይደለም። ይህች ሴት ጥሩ ሴት አይደለችም እያልኩ አይደለም፡ የጎዳና ተዳዳሪ ነች

ወይም ሌላ ነገር እያልኩ አይደለም። የኔ አመለካከት ይህ አይደለም። ነገሩ ግን፡ እዚህ ላይ ነው፡ ውጫዊው አካሏ ሰው ሰራሽ የሆኑ ብዙ ነገሮች ካደረገች፡ በውስጧም ሰው ሰራሽ ነገሮች መሞላቷ ያሳያል፡ አያችሁ፡ ግን'ኮ በክርስቶስ መሞላት የነበረባት ናት። በእርግጥም፡ ውጫዊው ክፍል ሁልጊዜ በውስጡ ያለውን ነገር ይገልጻል። "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።" አያችሁ? ክርስቶስም በሚኖርበት፡ ለእግዚአብሔርም ሊጨነቁ ሲገባቸው፡ ስለ ብዙ አርቴፊሻል ስለ ሌሎችች ነገሮች፡ ታውቃላችሁ፡ ስለ ግሪን ኩል፡ እና ኢ-ሰዋዊ መልክ፡ እና ይህ መሳይ አሸንክታቦች ይናፍቃሉ። ያን በፍፁም አልቀበልም፡ እና መፅሃፍ ቅዱስም ያንን ያፀድቃል ብዬ አላምንም፡ ስለዚህ እራሳችን እንድንሆን እወዳለሁ።

87 አስተውሉ፡ አሁን፡ ምንም ጥፍር ስለሌላት፡ እንዲኖራት የምትፈልግ ከሆነ፥ ምንም ጥርስ ስለሌላት፡ ማስተከል ከፈለገች፥ እጅ ስለሌላችሁ፡ እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ፥ ጸጉር ስለሌላችሁ፡ እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ፥ እነዚህ ነገሮች ስለሌሏችሁ ከሆነ፡ ሌላ ርዕሰ ነው። ነገር ግን መሆን ያለባቸውን ያህል ብሩህ ባለመሆናቸው፡ ጥሩ የተፈጥሮ ጥርሶቻችሁን ነቅላችሁ ስታወጡ ግን፡ ስህተት ታደርጋላችሁ። ቀይ ጸጉር ስላላችሁ፡ ጥቁር እንዲሆንላችሁ ስለፈለጋችሁ ብቻ፡ ሄዳችሁ ጥቁር ብትቀቡት፡ በዚህ ምክንያት ከሆነ፥ ስታችኋል። አዎን፡ እኔ የማስበው ይህ ነው። ከሁሉም በላይ ግን... ለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል የለውም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ያለው፡ ጸጉር ስለመቁረጥ፡ ብቻ ነው። አዎን፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ብዙ አሉ፡ ስለዚህ፡ ያ በጣም ግልጽ እንደሆነ እርግጠኛ መሆን አለብን።

88 ስለዚህ፡ እህታችን፡ በሕልሟ፡ እንዲህ አይነት ህልም አየች... እንግዲህ፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ደንግጣ ነበር። "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዲኖረን የሚፈልግ ከሆነ፡ እኛ ግን ከሌለን፡ ወደ ፊት መሄድ እና በህይወት ለመታገል መሞከር ምን ዋጋ አለው? " እንግዲህ፡ ምንም ያለው አይመስለኝም...

89 ይህንን እየቀዱት ሊሆን ይችላል። እየተቀዳ... እየተቀዳ ከሆነ ግን፡ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ብቻ ነው። አያችሁ? አሁን፡ ይህን ካሴት የሚቀበል የትኛውም ወንድማችን፡ ድምፄን ከሰማህ፡ ወንድሜ፡ ይህ፡ ይህ ትምህርት፡ ለቤተክርስቲያኔ ብቻ እንደሆነ አስታውሱ። ሁሌም እንዲህ አርጉ፡ ከጉባኤህ በፊት፡ ካ—ካሴቶቹን መገምገም ትችላላችሁ፡ እና ጉባኤህ እንዲሰማቸው ካልፈለጋችሁ፡ እንዲሰሟቸው አትፍቀዱላቸው። እኔ ግን እዚህ ላለው ታናሽ መንጋ ለመናገር እየሞከርኩ ነው፡ ይህም—እኔ እና ወንድም ነቪል፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ እረኛ በመሆን እና—በማስተማር የምንመራው መንጋ ነው።

90 እንግዲህ፡ በአንዳንድ ነገሮች ላይ ክፉኛ ላትስማሙ ትችላላችሁ። እንዲህ ከሆነም፡ ብዙዉን ጊዜ ፍራይድ ቺክን ስለመብላት ተናግሬአለሁ፡ "አጥንቱ ላይ ስትደርሱ፡ ደሮውን በሙሉ አትጥሉትም። አጥንቱን ትጥላላችሁ እንጂ።" ስለዚህ ሁሌም እንዲሁ አድርጉ። "የቼሪ ፓይ እየበላችሁ፡ ጥሬ ዘር ሲገጥማችሁ፡ ፓዩን አታሰወግዱትም። ዘሩን ብቻው ትጥሉታላችሁ።" ስለዚህ ይህንን ስታዳምጡ ተመሳሳይ ነገር አድርጉ።

91 እንግዲህ፡ በዛሬው ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ብዙ ግራ መጋባት የ—የተፈጠረው ም—ም—ምክንያት፡ እኔ እንደማምነው፡ ትምህርቱ በትክክል

ስላልተሰጠ ነው። ስለ ጥምቀት ትምህርት መስጠቱ እምናለሁ... ግን ለምሣሌ "ጥምቀት" እንበል።

92 ነገር ግን ለምሳሌ እስኪ "አውቶሞቢል" እንበል። አሁን በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ መካኒኮች አሉኝ፡ እኔ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳች እውቀት የለኝም። ስለዚህ ወንድሞቼ፡ ከተሳሳትኩ፡ እ... ሜካኒክ አለመሆኔን፡ አስታውሱ። አውቶሞቢሉን ሙሉ የሚያደርጉት ኮይሎች፡ እና መስኪያዎች፡ ክርኖች፡ ቫልቮች፡ እና ሌሎች ነገሮች በሙሉ፡ መኖር አለባቸው።

93 ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ስትናገሩም፡ ከዚህ ጋር የሚሄዱ ብዙ ነገሮች አሉት። እሺ? እያችሁ? ከሱ ጋር የሚሄዱ ብዙ ነገሮች አሉ። እግዚአብሔርም እያረጋገጠ ያለ ይመስለኛል፡ መንፈስ ቅዱስ እዚህ አለ። እያችሁ?

94 አሁን፡ ጴጥሮስ በመጀመሪያ፡ "እምነት" አለ። አሁን፡ ትኩረት ስጡ። ይህንን ለጥቂት ደቂቃዎች እንማራለን። መጀመሪያ፡ የሚያስፈልጋችሁ፡ እምነት ነው። በእምነታችሁም ላይ፡ በጎነትን ጨምሩ፥ በበጎነታችሁ፡ ዕውቀትን፥ በእውቀታችሁ፡ ራስን መግዛትን፥ በራስ መግዛታችሁ፡ ትዕግስት፥ በትዕግስታችሁ፡ እግዚአብሔርን መምሰል፥ እግዚአብሔርን በመምሰል፡ የወንድማማች ፍቅር፥ የወንድማማች መዋደድ ጨምሩ፥ ከዚያ በኋላ ፍቅር። ፍቅርም እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ ሁሉም ያውቃል። "እግዚአብሔር ፍቅር ነው።" እያችሁ?

95 አሁን፡ እንግዲህ፡ ከዚያ በመነሣት፡ ይህን ወደ ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት እናመጣዋለን። እግዚአብሔር በሰባት የቤተ ክርስቲያን ዘመናት፡ የክርስቶስ ሙሽራን ሠራት፥ በፊላደልፊያ፣ ትያጥሮን፣ በጴርጋሞን፣ በሰምርኔስ፣ እና በኤፌሶን ዘመናት ሁሉ። ስለ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "ሙ——ሙሽራው በመጀመሪያው ወይም በሰባተኛው ሰዓት ቢመጣ፡ እነዚህ ሁሉ ደናግል ይነቃሉ።" እነርሱም። የኤፌሶን ደናግል፣ የሰምርኔስ፣ የጴርጋሞስ፣ የትያጥሮን፣ የሰርዴስ፣ የፊልድልፍያ፣ እና የሎዶቅያ ደናግል፣ ነቁ። አስተውላችኋል? እነዚህን የተኙትን ደናግል መጥቶ የቀሰቀሳቸው፡ በሰባተኛው ዘመን ነው። ያም እነዚህን ሁሉ **እዚህ** ድረስ ያመጣቸዋል። እያችሁ? ይህም፡ በዚህ ውስጥ፣ በአመታት፣ በዘመናት፣ ሙሽሪትን ገንብቷል፣ ሙሽሪት ወልዷል፣ ለክርስቶስ በምድር ላይ ሙሽሪትን ወልዷል። እናም ይህችን ሙሽራ በወለደበት መንገድ፡ ግለሰቦችን ወልዷል።

96 የእህታችን ህልም ሲነገር እንድታዩት፡ አሁን ይህንን ዳራ አድርጌዋለሁ።

97 እንግዲህ፡ በመንፈስ ቅዱስ ከመታተማቸው በፊት ይሄኛው ወደ መደምደሚያ ራስ ወርዶ ሙሉ ወገን ከማድረጉ በፊት፡ እነዚህ ነገሮች በአንድ ክርስቲያን ሰው ላይ መሆን ይገባቸዋል።

98 አሁን፡ እህታችን ህልም አየች። ባሏ ጋዜጣ በሚያነብበት ሶፋ ላይ ተኝታ ሳለች፡ መንፈስ ቅዱስ አለኝ ወይስ የለኝም እያሰበች ትጨነቃለች ነበር። ልክ እኔ እንዳሉኝ፡ ህጻናት ልጆች አሏት፡ እነሱም ሁሌ ይንጫጫሉ ይረብሻሉ። ስለዚህ፡ በዚህ ነገር ላይ፡ በግምት ለአሰር፡ ወይም አስራ አምስት ደቂቃዎች ያህል ተኛች። እና ህልም አየች። ይህ መልእክት እስከተማርንበት ቀን ድረስ፡ ከአንድ አመት በላይ፡ ገደማ፡ ልትረዳው አልቻለችም፡ ሁሉንም አንድ ላይ ማስተሳሰር

አልቻለችም። ከዚያ በኋላ፡ እኔ ይህን እያስተማርኩ ሳለሁ፡ ሁሉም እንደገና ወደሷ ተመልሶ መጣ። እየጸለየች እንደሆነ በህልሟ አየች።

99 በመጀመሪያ፡ ህልም ከማየቷ በፊት፡ እጆቿን እያንቋቋች፡ እና እያሰበች፡ ወዲያና ወዲህ እየተንጎራደደች ነበር፡ “ጌታ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስ አለኝን? እቤቱ አረጋግጥልኝ። አንዳንዶች ‘በመጮኽ ነ—ነው፡’ ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ፡ ‘ልሳኖች በተናገረ ነው’ ይላሉ። እኛም እነዚህን ሁሉ እናምናለን። በእርግጥ እኔ ግን ተሞልቻለሁን? ”

100 በእነዚህ ሁሉ ነገሮች፡ በእነዚህ ቁመናዎች፡ ልሳኖችን በመናገር፡ በመጮህ፡ እና በሁሉም ዓይነት ማሳያዎች እምናለሁ። በዚህ ሁሉ እምናለሁ። ይህ ግን **ያለዚህ** ከሆነ፡ የሆነ ችግር አለ። አያችሁ? አሁን፡ ተመልከቱ፡ እዩት፡ ቅ—ቅርፊት አላችሁ። እስተውሉ።

101 በነገሩ ተጨነቀችና፡ ባሏ በሚያነብበት ሶፋ አጠገብ ላይ ጋደም አለች፡ እናም ተኛች።

102 ከዚያ በተራራ ራስ ላይ ሆና እራሷን አየች። እና በዚህ ተራራ፡ ዋናው... ወረቀቱን ከእኔ ጋር የለም፡ ቢሆንም እንዲህ ይመስለኛል። በሕልሟ የተራራው ጫፍ ላይ፡ ልክ—እንደ—ፍሬምዋርክ የተቀመጠ፡ የ—የድንጋይ ሣጥን፡ ባሏም ከኋላዋ ቆሞ ነበር። አንድ ትልቅ ሰውም፡ የሰራ ልብሰ ለብሶ ቆሞ ነበር፡ እጅጌው እንዲህ ጠቅልሎ፡ አይታ የማታውቀውን ንጹህ ውሃ፡ በዚህ ሣጥን ውስጥ ሲያፈስ አየችው፡ ይህም በተራራው አናት ላይ የተቀመጠውን የድንጋይ ሣጥን ነው። ይህ የድንጋይ ሣጥን ውኃውን መያዝ አልቻለም። በቀላሉ ከዚያ እየፈሰሰ ይወጣል፡ በዚያ አካባቢ የተገኘውን፡ ቆሻሻውን እና እንጨቶቹን ሁሉ ይቀቅላቸው ነበር፡ እንዲሁ እየቀቀላቸው ከተራራው ወደ ታች ይወርድ ነበር። በእግሯም ዙርያ ይፈስ ነበር፡ እሷም በዚያ በዕቃው አጠገብ ቆማ ነበር፡ ብቻ ከእሷ ጋር አልተጣበቀም ነበር።

103 እና—ከዚያም ሳጥኑ ሊይዘው ለምን እንዳልቻለ ጠየቀችው፡ ሰውየውም እንዲህ አላት፡ “ይህ ውኃ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ነው፡ እና፡” “ምንም ሊይዘው አይችልም፡” አላት። እሷም ተመልሶ ሄደና፡ ማር የሞላበትን፡ ሌላ ትልቅ ባልዲ አምጥቶ፡ ማሩንምም ወደዚያ ገለበጠውና፡ “አሁን ይህን ይይዛል” አለ፡ ትላለች። እሷም ይህ ሣጥን፡ የድንጋይ ሣጥን፡ እንደሚሰበር እና ማሩንም እንደሚያፈስው አሰበች፡ ይሁን እንጂ አልተሰበረም። በመጨረሻ ተጠባብቀው በደንብ ተያያዙ።

104 ዘወር ብላ ከተራራው መውረድ ጀመረች። ከተራራው ወርዳ፡ ከተራራው ስር ቆማ ወደ ኋላ ተመለከተች። እነሆ የዚህ ንፁህ፡ በማናቸውም ባለፈባቸው ነገሮች ያልተበከለ፡ ክሪስታል ንፁህ ውሃ አምስት ጅረቶች አየች፡ አሁንም ንጹህ እና ኩልል ያለ ሆኖ፡ በፍጥነት እየፈሰሰ ነበር። ከዚያም ፍሰቱ ቀዘቀዘ። ከዚያ በኋላ፡ ለመድረቅ ተቃረበ፡ እነዚህ አምስት ምንጮች፡ ለመሆኑ ከተራራው ግርጌ ይደርሱ ይሆን ብላ ማሰብ ጀመረች። ያን ጊዜ ነቃች።

105 እንግዲህ እውነታው ይህ ይመስለኛል፡ አይደል፡ እህት ሼፐርድ?

106 አሁን፡ ልክ ደብዳቤውን እንሰቴ ከከፈትኩት በኋላ፡ ሳላነበው፡ ህልሟን አየሁት።

107 ህልሞች የሚተረጎሙት በዚህ መንገድ ነው። አሁን፡ ብዙዎቻችሁ ህልሞች አይታችሁ ወደ እኔ መጥታችኋል፡ እ—እና ስለ ሕልም ነገሮች ነግራችሁኛ ታውቃላችሁ። እኔም፡ "ቆይ አንዴ። ሙሉውን አልነገርከኝም" ብያችሁ አውቃለሁ። አያችሁ? መለስ ብዬ እረዳዋለሁ። ስለዚህ ሕልሙን መናገር ካልቻላችሁ፡ ትርጉሙ ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንዴት ማወቅ ይችላሉ? አያችሁ? ሕልሙን ማየት፡ ማየት ይኖርባችኋል። ራዕይ ሕልሙን ማሳየት አለበት። እናም ሰውዬው ያየውን ሕልም ሰታዩ፡ እነሱ ከመናገራቸው በፊት መናገር ከቻላችሁ፡ ያን ጊዜ ትርጓሜውን ማወቅ ትችላላችሁ።

108 እንግዲህ፡ በመጽሀፍ ቅዱስ እንዲሁ፡ በአንድ ወቅት፡ በዳንኤል፡ ይህ እንደሆነ አምናለሁ። ልክ አይደለም ወይ? እ... አዎን። ይሄን ያሰብኩበትም ያን ጊዜ ይመስለኛል። አያችሁ?

109 ስለዚህ ህልሙ ትክክል የሚሆን ከሆነ፡ እንግዲህ፡ ሁልጊዜ ህልሙን አስቀድማችሁ ታዩታላችሁ። አንድ ሰው ሕልሙን ሊነግራችሁ ሲጀምር፡ ታስቆሙት እና፡ እንዲህ ትላላችሁ፡ "ቆይ አንዴ። ነገሩ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ነበር። **እንዲህ-እና-እንዲያ**፡ እንዲሁም **እንዲህ-እና-እንዲያ** ነበር።"

ከዚያም "ይህ ሁሉ እውነት ነው፡" ትሏቸዋላችሁ። አያችሁ?

110 በቀደም፡ አንድ ሰው፡ ያየውን ሕልም ሊነግረኝ እየሞከረ ነበር። እንዲህ አለኝ፡ "ይኸው ነው፡" አለኚ...

እኔም "ይኸውልህ፡ ወንድሜ፡ ይሄኛው ክፍል ለምን ተውከው፡" አልኩት?

እሱም "የትኛውን ክፍል፡" አለኝ?

111 እኔም "ድንጋዩን በአየር ላይ እንደወረወርክ፡ እኔም እንደተኮሰኩበት እና ዓይኔ ውስጥ እንደገባብኝ በህልም አይተሃል፡" አልኩት።

112 "ትክክል ነው፡ ወንድም ብራንሃም፡" አለኝ። የመጨረሻው ሰብርባሪ፡ ትናንትና አውጥተውልኛል። ኧሃ-ሃህ።

113 ይኸውልህ እንግዲህ። አያችሁ? አያችሁት? ለምንድነው? እውነቱን ሙሉ በሙሉ ባትናገሩትም፡ ነገሩ፡ ተመልከቱት፡ ወደ ኋላ መለስ ይልና ይገለጣል፡ ምኑን፡ ያለማችሁትን ህልም፡ ህልማችሁን ይነገራችኋል። ያን ጊዜ ትክክል መሆኑን ታውቃላችሁ።

114 አሁን፡ የሕልሟ ፍቺ ይህ ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ተጨንቃ ነበር። አሁን፡ ይህ በተራራው እናት ላይ ያየችው ሳጥን፡ ዓለት ነበር። የዓለት ሳጥን፡ **ድንጋይ** ነው፡ "የእንደበት ምስክርነት" ነበር። ማለት፡ ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለው ነው። ጴጥሮስን ሲናገር፡ እሱ እንዲህ አለው... "ማን ይሉኛል፡" "ሰዎች እኔ የሰው ልጅን፡ ማን እንደሆንኩ፡ ይሉኛል፡" ጠየቀ ኢየሱስ?

"እንዳንዱ አንተ 'ኤልያስ፡' 'ሙሴ፡' እና ሌሎችም ይሉሃል።"

"እናንተስ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ፡" አላቸው?

እርሱም፡ "አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" አለው።

115 አሁን፡ አንዳንዶች እንዲህ ይላሉ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ትላላለች፡ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ ማለትም የገነባው-... "ይህ ኢየሱስ የተናገረለት፡ ሰለ ዓለቱ ሲናገር፡ 'በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን

እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም’ አለ።” እነሱም እንዲህ ይላሉ፡ “**ጴጥሮስ** ማለት ትርጉሙ ‘ትንሽ ድንጋይ’ ማለት ሲሆን፡ ያንን ዓለት ጴጥሮስ ነበር። የተገነባውም በጴጥሮስ ላይ ነው። ‘በዚህች ትንሽ ድንጋይ ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ።’” ስለዚህ እነሱ፡ በጴጥሮስ ላይ፡ በሐዋርያዊ መተካካት፡ ቤተ ክርስቲያኒቱን ገነባናት ይላሉ።

116 የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ፡ “ይህ ስህትተ ነው። ቤተ ክርስቲያንን የገነባት፡ በራሱ ላይ ነው” ይላሉ።

117 እንግዲህ፡ በእኔ እይታም፡ ሁለቱም ስህተት ናቸው እላለሁ፡ ይህ ግን፡ እኔ፡ ላለመስማማት ፈልጌ አይደለም። ምክንያቱም፡ በጴጥሮስ ላይ፡ ወይም በራሱ ላይ በጭራሽ አልገነባትም፡ እሱ የገነባት እሱ ማን እንደ ሆነ በተገለጠለት በጴጥሮስ መገለጥ ላይ ነው። አያችሁ?

“ሰዎች እኔ የሰውን ልጅን፡ ማን እንደ ሆንሁ ይላሉ? ”

“አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ።”

118 “የዮና ልጅ፡ ስምዖን ሆይ፡ ብፁዕ ነህ። ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም፡” ሴሚናሪዎች አልገለጡልህም፡ አያችሁ፡ “በሰማያት ያለው አባቴ ገልጦልሃል። አንተ ጴጥሮስ ነህ። በዚህ የአንደበትህ ምስክርነት ዓለት ላይ፡ በዚህ መገለጥ ላይ፡ ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ።”

119 ከበፊት ጀምሮ፡ እያንዳንዲ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ እስከ አሁኗ ሎዶቅያ የአንደበት ምስክርነት ዓለት ድረስ ያንን የአንደበት ምስክርነት ዓለት ነበራቸው።

120 ስለዚህ፡ አሁን፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መገንባት አትችሉም። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወይም ቅዱስ ድርጅት ብሎ ነገር የለም። መንፈስ ቅዱስ በዚያ ይሰበካል፡ ቢሆንም በውስጧ ጥሩ ሰዎች እና መጥፎ ሰዎች፣ ከሃዲዎች፣ ግዴለሽ ሰዎች፣ እና ሁሉንም ነገር ታገኛላችሁ። ስለዚህ ድርጅት መደገፍ አይችልም። “ሌሎች ሁሉ አላገኟትም። እኛ አገኘናት፡” ማለት አትችሉም። በጭራሽ፡ ወዳጄ። መንፈስ ቅዱስ የሚፈሰው በግለሰቦች ላይ ነው። በግለሰቡ ነው።

121 እንግዲህ፡ ይህች፡ ዓለቷ፡ መንፈስ ቅዱስን የተቀበለችው የኋለኛዋ-ቀን፡ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን፡ ያኔ በመጀመሪያ እንደተቀበሉት ተቀብላለች። ስለዚህ በሁሉም ዘመናት፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል፡ ይሁን እንጂ አሁን በተቀበሉት መጠን አይደለም፡ ምክንያቱም ይሄኛው ወደ መጀምሪያው የሚያቃና ነው። ሰለ ወርቅ መቅረዞች ሰናያቸው፡ አልፋ እና ኦሜጋ ናቸው፡ የመጀመሪያዋ መቅረዝ ይለኩሷታል፥ ከዚያም ወደ ላይ እየጨመረ በሄደ ቁጥር፡ እየደበዘዘ ና እየደበዘዘ ይሄዳል፡ ከዚያም እንደገና ይመለሣል። አያችሁ? መጀመሪያ እና መጨረሻ፡ ወዘተ።

122 አሁን ግን፡ በዚህች የቤተክርስቲያን ዘመን፡ መልእክቱ ወደ ቸርች ፈሰሰ። ቸርች ራሷ ግን፡ የአካሉ ሰውነት ናት፡ በአጠቃላይ እንደ...

123 ስለዚህች ተበርናክል፡ ስንናገር። (ቸርች የሆነችበት ሰፍራ ያ ነው።) ይህች ተበርናክል የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አይደለችም። እንደዚህ ያለ ነገርም የለም። የመንፈስ ቅዱስ ማደርያዎች የምንላቸው ወደዚህ ቸርች የሚመጡ ግለሰቦችን

ነው። በአካል ዘንድ ያለች ቸርች፡ ወይም ቡድን ሳይሆን፡ መንፈስ ቅዱስን የያዙ ድንኳኖች ሰዎቹ ናቸው። ስለዚህ፡ መድረቅ ይጀምራል።

124 ነገር ግን፡ ይህ፡ ውኃን ሲገለብጥ የነበረው ሰው፡ የቤተክርስቲያኒቱ መልእክተኛ ነው፡ መልእክቱን ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ይገለብጥ ነበር፡ ውኃው ግን ምን እየሆነ ነበር? በውስጡ ያለውን ቆሻሻ ሁሉ እያፈላ ያወጣው ነበር። መንፈስ ቅዱስም የሚያደርገው ያ ነው፡ አሁን፡ አቃጥሎ ያወጣዋል።

125 እንግዲህ፡ ማር ማለት የወንድማማች ፍቅርን፣ የወንድማማች መዋደድ ተምሣሌት ነው፡ ማለትም ይህ ዘመኑን ይወክላል። አሁን ያለንበትን ዘመን፡ የወንድማማችነት መዋደድ፡ አያችሁ፡ በመንገር ነው።

126 አሁን፡ እንዲህ ልትሉ ትችላላችሁ፡ "ይኸውልህ፡ እ—እ—እኔ ወንድም ኔቪልን በፍጹም አልወደውም።" ወይም፡ "ወንድም ጆንሰን በፍጹም አልወደውም። ወንድም **እከሌ-እና-እከሌን** አልወደውም፡" እና የመሳሰሉትን ነገሮች ልትሉ ትችላላችሁ። እስኪ አንድ ነገር ይደርስበት፡ ወንድሜ፡ ያኔ ልብህ ይሰበራል። በጣም ትጎዳለህ። አያችሁ? እርስ በርሳችን ወንድማዊ መዋደድ እና ስሜት ሊኖረን ይችላል። አያችሁ? በሰዎች ማሕበር መካከል ይህን መጠበቅ ግን...

127 ለዚያ ወንድም ስለምን ትጨነቅለታለህ? ምክንያቱም ዛሬ ማታ እንደምታደርጉት፡ በዚህ በመሠዊያው ላይ ከእርሱ ጋር እንጀራ ቆርሳችኋል። ከእሱ ጋር ሕብረት አድርገሃል። እጁን ጨብጠሃል። ከእርሱ ጋር አምልከሃል። ወንድምህ ነው። አንተ የማትስማማውን፡ በሥጋ የሆነ ነገር ሊያደርግ ይችል ይሆናል፡ ከዚያም ትርቀዋለህ፡ (ይህ ማድረግ የሌለብህ ነው)፡ በጥቂቱ ግን ቆጠብ ትላለህ። በልብህ ውስጥ ግን፡ በዚያ ወንድም፡ ወይም በዚያች እህት ላይ የሆነ ነገር ቢደርስ፡ ልብህ ይሰበራል።

128 እ—እኔ ሽማግሌ ነኝ። ወጣት ነበርኩ፡ አሁን አርጅቻለሁ። በዚህ ዘመን ሁሉ፡ ይህ ሲከሰት፡ አይቻለሁ። ሰዎች "ከእሱ ጋር ምንም ግንኙነት እንዲኖረኝ በፍጹም አልፈልግም፡" ሲሉ እሰማቸዋለሁ። ከዚያ በኋላ ያ ሰው አንድ ነገር ሲደርስበት፡ ልቡ ይሰባበራል። "አምላክ ሆይ፡ ከሱ ጋር ሳልታረቅ፡ ውድ ወንድሜን አጣሁት፡" ብሎ ማሰብ ይጀምራል። አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ? ይህ የወንድማማችነት ፍቅር ነው። የማይጣበቅ ይመስላል እንጂ፡ ይጣበቃል። ማር፡ ይጣበቃል።

129 እንግዲህ፡ ከዚያ መምጣቷ ማለት፡ ከኮረብታው፡ ወደ ኮረብታው ግርጌ መውረዷ፡ ማለት፡ ይህ የከበረ ውኃ፡ በአምስት ጅረቶች ውስጥ ባሉ ኮረብቶች ላይ ይፈስ ነበር። አሁን፡ አምስት የጸጋው ቁጥር ነው፣ J-e-s-u-s፣ f-a-i-t-h፣ g-r-a-c-e። አያችሁ? አምስት የጸጋ ቁጥር ነው። አምስት ጅረቶች ከዚህ ወደ ታች፡ **ወደዚህ** ዲች ይፈሱ ነበር።

130 በእነዚያ ዘመናት ውስጥ እያንዳንዱ ዘመን የእንደበት ምስክር ዓላት ነበራቸው። ቅዱሳኑ እስከዚህ ዘመን ድረስ ተኝተው፣ እየጠበቁ፣ እየጠበቁ፣ እየጠበቁ፣ አያችሁ፡ እስከዚህ ዘመን ድረስ፡ እየጠበቁ ይገኛሉ። መንፈስ ቅዱስ ግን በቅርቡ፡ ከክርስቶስ የፈሰሰ በመሆኑ፡ መጥቶ ቤተክርስቲያንን ያትማታል። ያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ትነጠቃለች። ያን ጊዜ የሁሉም ራስ የሆነው፡ የክርስቶስ

ሙሽሪት የሆነች፡ የእግዚአብሔር ሙሉ ወገን ትሆናለች። አሁን ተከታተሉኝ? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።]

131 አሁን፡ እሷ ጥያቄ ሆነባት። እናም፡ በህልሟ፡ እራሷን ይህንን ጥያቄ ጠየቀች፡- "ይህ ትንሽ ጅረት... ይህ ትንሽ ጅረት ወደ ታች ይደርስ ይሆን?" አያችሁ? እየደረቀ ነበር። ስለዚህ፡ ይህ ሲሆን፡ ስለ ራሷ ነው። ስለሆነ እንድትረዱት የምፈልገው ነገር ይኸውና። እሷ ራሷ ስለራሷ እያሰበች ነበር። "መንፈስ ቅዱስ አለኝን፡" ብላ ተደነቀች?

132 እንግዲህ፡ ከጥቂት ቀናት በፊት፡ ቤተ ክርስቲያን በቂ መንፈሳዊት ስለሆነች፡ ይህን ራሷ ትደርስበታለች በሚል ይህን ከመናገር ተቆጠቤአለሁ። እና ምናልባት ይህ በወንድማማቾች መካከል እንዲፈጠር ስለማልፈልግ፡ ቀረጻውን አሁኑኑ ባቆመው ይሻለኛል። ቢሆንም በልሳኖች መናገር፣ መጮህ፣ መደነስ፣ አጋንንትን ማስወጣት፣ የፈለጋችሁትን ማድረግ ትችላላችሁ፡ በዚህ ሁሉ ግን መንፈስ ቅዱስ ላይኖራችሁ ይችላል።

133 ደቀ መዛሙርቱስ አጋንንት ስለ ተገዙላቸው፡ ደስ እያላቸውና እየጮኹ አልተመለሱምን፡ ኢየሱስ... ይሁዳስ ራሱ በመካከላቸው አልነበረምን?

134 ኢየሱስስ፡ "በዚያን ቀን" እሱ ሲመለስ፡ "ብዙዎች ወደ እኔ ይመጣሉ፣ 'ጌታ ሆይ፣ በስምህ አጋንንትን አላወጣሁምን፣ ተአምራትንም አላደረግሁምን ይላሉ አላለምን?' እኔም 'እናንተ ዓመፀኞች፡ ከእኔ ራቁ። አላወቅኋችሁም፡' እላቸዋለሁ።" እነዚህ ነገሮች የመንፈስ ቅዱስ ምልክቶች አይደሉም።

ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።

135 እናንተ እንዲህ ትሉኛላችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡በልሳኖች፡ እንናገርን? ያለ ጥርጥር። እነዚህ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ስጦታዎች፡ ያለ እነዚያ ቁመናዎች፡ ለማያምን ሰው እንቅፋት ይፈጥራሉ። ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

136 ቅድሚያ እነዚያ መኖር አለባቸው። እምነት፣ በጎነት፣ እውቀት፣ ራስን መግዛት፣ መጽናት፣ እግዚአብሔርን መምሰል እና የወንድማማች ፍቅር ሲኖራችሁ፣ ያን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ዘመናትን እንደ አንድ ወገን አድርጎ እንዳተማቸው፡ መንፈስ ቅዱስም ወርዶ እንደ አንድ ወገን በማኅተም ያትማችኋል። ሙሽራውን በሚያበጅበት መንገድ ግለሰቡን የሚያበጅበት መንገድም ያው ነው፥ ልክ ሄዋንን ከአዳም፡ ከጎኑ አጥንት እንዳበጃት ሁሉ፡ ከአንዱ አይነት ንጥረ ነገር ያበጃዋል። ቅድሚያ ሊኖሯቸው የሚገቡ ነገሮች **እነዚህ** ናቸው። እነሱን ማስመሰል አትችሉም። እነሱን መምሰል አትችሉም። ከእግዚአብሔር-የተላኩ እና ከእግዚአብሔር-የተወለዱ መሆን አለባቸው። ማስመሰል ግራ መጋባትን ብቻ ያመጣል።

137 ልክ እንዳልኩት ነው። ጥንብ አንሣ የርግብ ላባ በክንፎቹ ውስጥ ሰካክቶ፡ "እነሆ፡ እኔ ርግብ ነኝ" ሲል፡ በሕሊናችሁ ሳሉት! እርግብ አይደለም። ጥንብ አንሣ፡ አሞራ ነው። ቁራ በክንፎቹ ውስጥ የፒኮክ ላባ ሰካክቶ፡ "እዩኝ!" ሲል፡ እስኪ በሕሊናችሁ ሳሉት? የተቀረቀረበት ነገር ነው።

138 ነገር ግን ከውስጥ ወደ ውጭ የሚወጣ ይሁን፡ ያኔ እግዚአብሔር፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ ክርስትናን ያፈራል!

139 እህታችን ወደ ታች ስትወርድ እግሯ ረጥቦ ነበር። እህት ሼፐርድን ሁላችንም የምናውቃት በበጎ አድራጊነቷ ነው። ቤቷ ክፍት ነው። እሷ እና ወንድማችን፡ አለሌ ሰው ይሁን፡ ለማኝ ይሁን፡ ወይም ምንም አይነት ሰው ይሁን፡ ይመግቡታል፡ እሱን ለመርዳት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። ኦህ! እግዚአብሔር ያንን፡ የመሠረቷን ክፍል ተቀብሏል።

140 እነሆ፡ አሁንም፡ ይህን ትምህርት ተረዱት። እዚህ ጋር ችግሩ ያለው—በ... በዚህ ነገር ላይ ጎላ ላድርገው። የብራንሃም ተበርናክል ችግር ይህ ነው። አያችሁ፡ ሁለት ዓይነት እምነት አለ። ባለፈው ቀን እንዳልኩት፡ ሁለት አይነት በጎነት አለ። ሁለት ዓይነት እውቀት። ሁለት ዓይነት መጽናት።

141 አንዳንድ ሰው፡ ይህ የተከለከለ ነው በማለት ያስባል። እግዚአብሔር እየተናገረ ያለው እንዲህ ዓይነት ራስን መግዛት አይደለም። ፈጣን ምላሽ እንድትሰጥ፡ እንድትጣላ የሚያደርግህ፡ ፈሪሃ እግዚአብሄር የሌለው፡ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ቁጣህ፡ እና የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው።

142 እነ መጽናት፡ እና ሌሎች ሁሉ፡ እነሱን የሚሳለቁባቸው፡ እነርሱን የሚመስሉ ማስመሰያዎች አሉ፥ ማለት በተፈጥሮ-የሚሰጥ እምነት አለ፥ እና በተፈጥሮ-የሚሰጥ በጎነትም አለ። በተፈጥሮ-የሚሰጠን መጽናት አለ። እነዚህ ሁሉ ነገሮች በተፈጥሮ የተሰጡ ናቸው።

143 እና የእምነታችን ትልቁ ክፍል የአዕምሮ እምነት ነው። ቃሉን ማዳመጥ፡ እግዚአብሔርን በአእምሯዊ እውቅና እንድናውቀው ያደርገናል።

144 ነገር ግን፡ ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ከላይ የሚመጣው፡ **ይህ** አንዴ ከነካህ ግን፡ አምላካዊ የሆነ መንፈሳዊ እምነት ይኖርሃል። ይህ አይነቱ እምነትስ ድርጊቱ ምንድነው? ይህ እምነት የሚያውቀው ቃሉን ብቻ ነው። ሌላው ምንም ቢናገር፡ ይህ እምነት የሚያውቀው ቃሉን ብቻ ነው፡ ምክንያቱም፡ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።" ቃሉ አሁንም እግዚአብሔር ነው። "ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።" እናም ቃሉ ራሱ ወደ እምነታችን ሲፈስ፡ የአዕምሮ እምነታችን መንፈሳዊ መገለጥ ይሆናል።

145 "እናም በዚህ መሠረት ላይ ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ።" አያችሁ? በአእምሮአዊ ፅንሰ ሀሳብ በሚሆን፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመቀላቀል ሳይሆን፡ እነዚያ የጸጋ ጅረቶች ወደ አእምሯዊ እምነታችሁ መፍሰስ ሲጀምሩ፡ በምታገኟቸው መገለጥ ላይ የተመሰረተ ነው። ስለዚህም፡ በዚህ፡ በመንፈሳዊ መገለጥ "ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።" አያችሁ? ይህ የሚያሳየው እንደሚቃወሟት ሲሆን፡ ቢሆንም መቼም አያሸንፏትም ነው። ኦህ፡ እንዴት ያለ ክብር ነው! አሁን እምነትን ተመልከቱት። እነዚህ አምስት ጅረቶች...

እዚህ ጋር አንድ ቁራጭ ቾክ ነበረኝ፡ ቢሆንም አላጎላውም መሰለኝ።

146 እነዚህ የሚፈሱት አምስቱ ጅረቶች ግን፡ **ይህ** ሁሉንም አንድ ላይ ያጣምሩታል። የኤፌሶን ቤተክርስቲያንን የመሰረታት መንፈስ ቅዱስ ነው። የሰምርኔስ ቤተክርስቲያንን የወለዳት መንፈስ ቅዱስ ነው። የጴርጋሞስን ቤተ ክርስቲያን፡ እና የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን፡ በጨለማው ዘመን ያፈራው መንፈስ ቅዱስ ነው። ካለፉት ከእያዳንዱ ዘመናት ከድርጅታዊ ሥርዓቶች ሁሉ አውጥቶ፡ እንዲሁ፡ ይህችን ሙሽራ የሠራት መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ምርጦች

በማለት የሚያውቃቸው፡ አስቀድመው የተወሰኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ፡ የተመረጡ አሉ። እንግዲህ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ነው **በዚህ** ዘመን፣ **በዚያ** ዘመን፣ **በዚያ** ዘመን፣ **በዚያ፣ በዚያ፣ በዚያ፣ በዚያ፣** እስከ ላይኛው ድረስ ያለው፣ መንፈስ ቅዱስ ነው።

147 እና አሁን እንደግለሰቦች፡ እነዚህ ቁመናዎች እና ነገሮች፡ እውቀት እና ራስን መግዛት ሁሉ፡ በእምነታችን ላይ የሚጨመሩ ናቸው። ከዚያ በኋላ የመደምደሚያው ድንጋይ ሲመጣ፡ መንፈስ ቅዱስ በደንብ ይመርገዋል። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ዛሬ በጣም ብርቅ የሆነው ለዚህ ነው።

148 እዚህ ጋር ስመለከት፡ አንዳንድ የተጻፉ ማስታወሻዎች ይዣለሁ። እንመልከተው፡ እሷ ያየችው ህልም ላይ፡ የሳልኩት አንድ ምሰል አለ። አያችሁ? ከዚያ ሆናችሁ አይታያችሁም።

149 እንግዲህ፡ ከመንፈስ ቅዱስ የሚመጣው፡ ምን ይመጣል? ያን ጊዜ **እዚህ** ግርጌ ስር፡ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ እምነት፡ መንፈሳዊ እምነት፡ ይሰጣችኋል። ከዚያም ይህ መንፈሳዊ እምነት የሚያውቀው ቃሉን ብቻ ነው። ማንም የፈለገውን ቢናገር፡ ጥቅም የለውም——ምንም አይጠቅምም። ቃሉን ብቻ ያውቃል። አንድ ሰው፡ "የተአምራት ዘመን አልፏል" ብሎ ይናገራል። እምነት የሚያውቀው ቃሉን ብቻ ነው። ሌላ ሰውም፡ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ብሎ ነገር የለም" ይላል። እምነት የሚያውቀው ቃሉን ብቻ ነው። እውነተኛው፡ መንፈሳዊ እምነት ያ ነው፡ አያችሁ። በትክክል። አያችሁ? የሚያውቀው ቃሉን ብቻ ነው።

150 ስለዚህ፡ ያ አንደኛው ቁጥር ነው። ቁጥር አንድ፡ ወደ እናንተ የሚመጣው፡ ይህ አእምሯዊ እምነታችሁ ላይ፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ አእምሯዊ እምነታችሁ ይመጣል፡ መንፈሳዊ እምነት ያደርገዋል። ያን ጊዜ መንፈሳዊ የሆነው እምነት ቃሉን ብቻ ያውቃል።

151 በመቀጠል፡ ቁጥር ሁለት፡ ሶስት። በዚያን ጊዜ መንፈሳዊ ትሆናላችሁ፡ መንፈስ ቅዱስም ይሆንላችኋል፡ **እነዚህን** ሁሉ በእናንተ ውስጥ ያትማል፡ መንፈስ ቅዱስ **ይህንን** ያጠቃልላል። ከእምነታችሁ፡ እስከ መንፈስ ቅዱስ ድረስ፡ ከክርስቶስ ጋር ያትማችኋል። ያኔ አንድ ትሆናላችሁ። ኣሜን። (ይህን ከፊቴ ዞር አርግልኝ፡ በእጆችህም ይከብድሃል።) አንድ ትሆናላችሁ። አየህ፡ አንተ እና ክርስቶስ አብራችሁ ትኖራላችሁ። "እኔ በአብ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ እንዳለ፡ እኔም በእናንተ እንዳለሁ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፡ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ።" አያችሁ? ስለዚህ የጌታ የእግዚአብሔር የታተመው ወገን ይህ ነው።

152 እነሱም፡ የተረጋገጡ ሆነው ርስታቸው ላይ ተቀምጠዋል። ያ ጊዜ ሲደርስ፡ የተረጋገጡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይሆናሉ።

153 በማቴዎስ መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 17 ላይ፡ ከቁጥር 1 እስከ ቁጥር 5 ድረስ፡ ኢየሱስ፡ በታቦር ተራራ ላይ ትዝ ይላችኋል?

154 **እርሱን ስሙት** የሚለውን ስብከት ሰምታችሁታል። ይህ **እርሱን ስሙት፡** የተባለው ስብከት፡ የዛሬ ዓመት አካባቢ፡ የሰበክኩት፡ እጅግ የታወቀ ሆኗል። በተጨማሪም በኤፌሶን 1፡5 ላይ፡ ልጅን በርስቱ ስለማስቀመጥ፡ "እግዚአብሔር አስቀድሞ ልጆች ልንሆነው ወስኖናል።

155 ተመልከቱ፡ አንድ ቤተሰብ፡ ያኔ ወንድ ልጅ በቤተሰብ ውስጥ ሲወለድላቸው፡ ወዲያውኑ ልጅ ይሆናል። ያ ልጅ ግን የሚያሳድጉት ሞግዚቶች ነበሩት። ልጁም ልጅ የሚያስብለው—የልጅ ትክክለኛ ቁመና ካላዳበረ፡ ፈጽሞ ወራሽ አይሆንም። የተስተካከለ ልጅ ከሆነ፡ እና አባቱን የሚታዘዝ ልጅ ከሆነ ግን፡ ያን ጊዜ በሙሉ ልጅነት ይረከበዋል፡ ወይም በርስቱ ይቀመጣል። የአባቱ የሆነውን ሁሉ ወራሽ ይሆናል።

156 እግዚአብሔርም በታቦር ተራራ ላይ ያደረገው ይህንኑ ነው። የገዛ ልጁን ሲወስድ፡ ይኸውላችሁ፡ ፈተናዎቹን ሁሉ ተቋቁሞ፡ መልካም ልጅ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ፡ ወደ ታቦር ተራራ አወጣውና በላዩ ላይ ጸለለበት።

157 ታውቃላችሁ፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን፡ ወንዱን ልጅ ወስደው፡ ባማረ ልብስ፡ በልዩ መልክ ያለብሱትና፡ በሕዝብ ፊት ያቀርቡት ነበር። ከዚያ በኋላ አሁን ማደጎ ብለን የምንጠራው፡ የርስቱን ሰፍራ የማስያዝ ሥነ ሰርዓት ነበራቸው። ጳውሎስ በገላትያ ላይ፡ ስለዚህ ነገር ሲናገር ልጆች እንሆነው ዘንድ በማለት የሚያስቀምጠው ይመስለኛል። አሁን ግን፡ ወንድ ልጅን በርስቱ ማስቀመጥ፡ አገልጋዮች፣ እና መንፈሳዊ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች የሆናችሁ፡ ልጅን በርስቱ ስለማስቀመጥ ታውቃላችሁ። በሌላ አነጋገር፡ ልጁ ልጅ የሆነው ሲወለድ ነበር።

158 የኛ ጴንጤዎች የሚሳሳቱት እዚህ ላይ ነው። ወደ ቤተሰብ፡ በመንፈስ ቅዱስ መወለድ፡ ትክክል ነው፡ ነገር ግን በትክክለኛ ሞግዚት ስር የተማሩና፡ ባለ ትክክለኛ ቁመና ልጆች መሆን ይጠበቅብናል። አያችሁ?

159 ለምሣሌ፡ በጥንት ዘመን፡ አንድ ሰው ስለ ልጁ ቢያስብ፡ እና ጥሩ ልጅ እንዲሆንለት ከፈለገ፡ አለ የተባለውን ሞግዚት፣ አስተማሪ ይፈልግለታል፡ ምክንያቱ ልጁ እንደ አባቱ እንዲመስልለት ይፈልገዋል። አያችሁ? ስለዚህ ትክክለኛውን ሞግዚት ያመጣለታል።

160 እንግዲህ፡ ምድራዊ ሰው እጅግ የተሻለ የሚለውን ሞግዚት መምረጥ ከቻለ፡ አባታችንስ፡ እግዚአብሔርስ ታዲያ? እንግዲህ፡ እሱ ቢሾፖችን፣ ካርርዲናሎችን፣ እና ቄሶችን አያመጣልንም። ሞግዚታችን ይሆን ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ያመጣል። መንፈስ ቅዱስም መምህራችን ነው። እ—እርሱም በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ነው፡ መልእክትም ወደ አብ ያስተላልፋል።

161 ታዲያ እንዲህ ከሆነስ፡ ይህ አባት፡ ማለቴ ይህ ሞግዚት እንዲህ ቢልስ፡ "ይኸውልህ፡ አባቴ... " አሁን፡ ኮፍያው ላይ ሰንጥር፡ ወይም፡ ላባ የምንለውን ነገር የሚሰካ አይነት ሞግዚት፡ አያመጣልንም። እንዲህ ቢል፡ "ኦህ፡ ይህን ነገር ለአባቱ ብነግረውስ... በመሰረቱም፡ ልጁ'ኮ ምናምንቴ ነው፡ አባቱን እንዲህ እና እንዲያ ካ—ካልኩት፡ አባትዬው እድገት ሊጨምርልኝ ይችላል።" ይህ አይነቱ ሞግዚት ትክክለኛ አይደለም። ትክክለኛ ሞግዚት ቅን ነው፡ እውነትንም ይናገራል።

162 መንፈስ ቅዱስም፡ ስለ እኛ ወደ እግዚአብሔር ፊት ሲቀርብ፡ እውነትን ይናገራል። አዎን። ስለዚህ ይቀርባል። ምን ይመስልሃል ይባላል? ዛሬ ይህን ለማናገር ይሳቀቃል፦ "ሴቶች ልጆችህ በሙሉ ጸጉራቸውን ይቆራርጣሉ፡ አንተ ግን እንዳይቆርጡ አዘሃቸዋል። ወንዶች ልጆችህ እጅግ ራስ-ተኮር ከመሆናቸው የተነሣ፡ እርስ በርስ አይጠያየቁም። በትክክል። **ይህንን** በዚህ ፈንታ፡ **ይህንንም**

በዚያ ፈንታ ተክተዋል። አቤት እንዴት ይሳቀቅ ይሆን! በአንጻሩም ይህ ሞግዚት መጥቶ እንዲህ ሲናገር እጅግ ደስ ይለዋል “አቤት፡ አቤት! ይህ ልጅህ እውነተኛ ልጅ ነው። እርሱ በእውነት እንደ አባቱ ነው።” ኦህ፡ እንደዚያ ማለት ደስ ሲለው! አያችሁ?

ያን ጊዜ አባቱ፡ “ይህ ልጄ ነው” በማለት፡ ኩራት ኩራት ይለዋል!

163 እግዚአብሔር በታቦር ተራራ ላይ ያደረገውም ይህ ነው። አስተውሉ፡ በዚያ ሙሴ እና ኤልያስ ታዩ። ጴጥሮስ፡ እና ሌሎቹም እጅግ ደስ አላቸው፥ መለኮታዊ ነገሮች ተከናወኑ። ጴጥሮስ እጅግ ደስ ስላለው፡ እንዲህ አለ፦ “በዚህ ሶስት ዳሶችን እንስራ፡ አንዱ ለአንተ፣ አንዱም ለሙሴ፣ አንዱም ለኤልያስ።”

164 እርሱም ገና ሲነገር ሳለ፡ እግዚአብሔር ዝም አሰባለው። “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው። እሱን ስሙት፡” አላቸው። አያችሁ? እግዚአብሔርም ራሱን ከበሰተጀርባ ሰወረና፡ “ይህ ልጄ ነው፡” አለ።

165 ሙሴ ሕጉን የሚወክል ነበር። ነብያትም ፍርዱን ይወክላሉ። እኛ ግን በሕጉ መኖር አልቻልንም። በፍርዱም መኖር ተሳነን። ፍርዱን አልጠይቀውም። ፍርዱ ሳይሆን፡ ምሕረቱን እሻለሁ። ህጉን መጠበቅ አልችልም፣ ፍርዱንም ማሟላት አልችልም። እኔ ግን ምህረቱን እሻለሁ። እርሱ ሕጉን እና ፍርዱ ማሟላቱን እግዚአብሔር መሰከረለት። “እርሱ የምወደው ልጄ ነው። እሱን ስሙት። እሱ ነው። እሱ ራሱ ነው።”

166 አሁን፡ በብሉይ ኪዳን ያ ልጅ በማደጎ ልጅ ለመባል ሲደርስ፡ ወይም የቤተሰብ አባል ስለመሆኑ ሲታወጅ፡ ከዚያ በኋላ የእሱ ስም በቼኩ ላይ እንደሚጻፍ እንደ አባቱ ስም አንድ ይሆናል። አዎን፡ ወዳጄ። አንድ ያልነበራቸው ነገር... ያኔ በዚያ ዘመን፡ እንደ—ምልክት፡ እንደ ማኅተም፡ ቀለበት ነበራቸው። እንዲህ ያደርጋሉ... [ወንድም ብራንሃም የመትፋት ድምጽ አሰማና መድረኩን መታው—አርታዒ።] ትፍ ትፍ ይሉበትና፡ ያጠልቁለታል፡ ማሕተሙም ያ ነበር። ልክ እንደዚያው ነበር... የአባቱን ቀለበት፡ ማሕተሙን ያጠልቃል። ያ ማለት ልክ እንደ አባቱ ሆነ ነው።

167 ስለዚህ፡ ኢየሱስም፡ ኢየሱስን ለእግዚአብሔር ታዛዥ ነበረ፡ እግዚአብሔርም “እነሆ እርሱ ነው” በማለት፡ በርሰቱ አሰቀመጠው።

168 አሁን፡ አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ሲወለድ እና እነዚህ ሁሉ ቁመናዎች በእርሱ ውስጥ እንዳሉ፡ እና እግዚአብሔር በጎነትን፣ እውቀትን፣ ራስን መግዛትን፣ መጽናትን፣ የወንድማማች መዋደድን፣ እግዚአብሔርን መምሰልም ያሉት መሆኑን ሲያረጋግጥ፡ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ማሕተሙን ያሳርፍበታል፡ ወይም በርሰቱ ያሰቀምጠዋል። እና፡ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ማየት የምትችሉት፡ በዚያ ነው።

169 ስለዚህ ኤፌሶን 4፡30 “እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ የታተማችሁበትን፡ ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ” ይላል። እንግዲህ፡ እናንተ ዘለአለማዊ ደህንነት በሚል ነገር መወሰድ የምትፈልጉ ባፕቲስቶች ሆይ፡ አሁን፡ ወደዚህ ደረጃ ላይ መድረስ ከቻላችሁ፡ ወደዚያ ርሰት ላይ ከመጣችሁ፡ እነሆ በዘለአለማዊ ደህንነት ከእናንተ ጋር እወግናለሁ።

170 ነገር ግን አንድ ሰው፡ እንዲሁ ተነስሥቶ፡ "እኔ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን አባል ሆኛለሁ። እኔ ፕሪስባይቴሪያን ነኝ። ዘለአለማዊ ደህንነት አለኝ" ይላል። ይህ ስህተት ነው። እነዚህ ነገሮች እስኪሆኑላችሁ ድረስ፡ ገና እንዳልደረሳችሁበት የገዛ ህይወታችሁ ይመሰክርባችኋል።

171 እግዚአብሔርም እናንተን ተቀብሎ በመንፈስ ቅዱስ ወደ መንግሥቱ ካተማችሁ በኋላ፡ ከዚያ መውጫ የላችሁም። ለዘለአለም የተጠበቃችሁ ትሆናላችሁ። እመኑ። "እናንተንና መለኮታዊ ቁመናዎቻችሁ ሁሉ እስከ ቤዛ ቀን ድረስ የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።"

172 አስቀድማ የተወሰነች ሙሽራ እንዳለች እምናለሁ። እግዚአብሔር "እድፍ ወይም የፊት መጨማደድ የሌለባት ቤተክርስቲያን" እንደምትኖረው ተናግሯል ብዬ አምናለሁ። አስቀድሞ በመወሰን አምናለሁ፡ ሙሽራይቱ አስቀድማ የተወሰነች ናት። እሷም እዚያ ደርሳለች። እኔም ከእሷ ጋር እንደሆንኩ ተስፋ አደርጋለሁ። ይኸው፡ ተመልከቷት፡ እኔም አካሏ ነኝ። እንግዲህ **እነዚህ** ነገሮች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን እስኪያገኙ ድረስ፥ የራሴን መዳን በእግዚአብሔር ዘንድ የምፈጽመው እኔው ነኝ፡ ከዚያ በኋላ ወደ እግዚአብሔር መንግስት እታተማለሁ። መንፈስ ቅዱስ ይህ ነው። የእግዚአብሔር እውነተኛው ሥራ ይህ ነው። "እስከ ቤዛነት ቀን ድረስ የታተመ ይሆናል።"

ህልሟ ይህ ነበር። ድንቅ እንደሆነ እስባለሁ።

173 እንግዲህ፡ ግለሰቡ፡ ወይም ቤተክርስቲያን፡ ይህንን ስታደርግ፡ ወደዚህ አይነት ደረጃ ስትደርስ፡ ቤተ ክርስቲያን እዚህ መድረስ ይጠበቅባታል። እንድትረዱት ይህን በግልፅ ልናገረው። ቤተክርስቲያ እዚህ ላይ መድረስ እንድትችል አስቀድማ ተወሰናለች። እኔም ከእሷ ጋር መቆጠር እፈልጋለሁ፡ ከእሷ ጋር የምቆጠርበት ብቸኛው መንገድ፡ አካሏ በመሆን ነው። የሷ አካል የምሆነው እንዴት ነው? በውስጧ በመሆን። ወደ ውስጧስ እንዴት እገባለሁ? በጥምቀት፡ በአንድ መንፈስ። አንደኛ ቆሮንቶስ 12 ላይ፡ "በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።" አንድ አካል፥ ወደዚያ አካል ተጠምቀናል።

174 ጥቃቅን ነገሮች በራሳችሁ ስካክታችሁ፡ "በልሳኖች ተናግሬአለሁ። ደርሼበታለሁ፡" ማለት ግን አትችሉም። ከዚያ በኋላ ትወጡና፡ ትቆጣላችሁ፣ ትምላላችሁ፣ ትሳደባላችሁ። አያችሁ? በ—በመስቀል ወፍ ላይ የፒኮክ ላባዎችን መስካካት ማለት ይህ ነው። አያችሁ? አይሆንላችሁም። የገዛ ህይወታችሁ እንዳልሆናችሁ ይመሰክርባችኋል።

175 ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በእናንተ ውስጥ ሆነው ሲሰሩ፡ ያኔ፡ በእግዚአብሔር ትታተማላችሁ። እንግዲያውስ ሌላ-ለጠፍ አያስፈልገውም። የራሳችሁ ሆናችሁ። ያን ጊዜ፡ ከክርስቶስ ጋር፡ ፍጹም፡ አንድ ስለሆናችሁ፡ ራእዮች፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እና ሌላው ሁሉ (ምን? ) የእግዚአብሔር ስራ ሁሉ መገለጥ ይጀምራል። ግልጽ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። እናንተ ኣና ክርስቶስ አንድ ትሆናላችሁ።

176 በዚህ ላይ የኔን ነጸብራቅ ማድረግ የምፈልገው፡ ሌላ ነገር አስተውዬ ነበር። ይህ ሕይወት ወዳለችበት ቦታ ያደርስናል። ያኔ ምን ትሆናላችሁ… የዘላለም ሕይወት ታገኛላችሁ።

177 እንግዲህ፡ እዚህ ጋር **ዘ ኢምፋቲክ ዲያግሎት፡** የሚባለውን የግሪክ መዝገበ ቃላት እዚህ ጋር ይዣላሁ። በቀደም አንድ ቃል እያጠናሁ ነበር።

178 አሁን፡ በዮሐንስ 14፣ ወይም ዮሐንስ 3፡16፣ አንድ ሰፍራ ላይ፡ "**የዘመናት** ሕይወት አለው፡" የሚል እንዳለ እናገኛለን። በሌላ ቦታ ደግሞ፡ "**የዘላለም** ሕይወት አለው" ይላል። ነገር ግን በግሪክ፡ በግሪክ ቅጂ ግን... ወይም በዕብራይስጥ፡ "ማለቂያ የለሽ ሕይወት፡" ይላል። የግሪክኛ ቃል፡ a-i-n-i-o-a-n ተብሎ ተጽፏል።

179 ልክ እንደ "**ኤዮን**" ነው። **ኤዮን** ማለት በቁጥር የማይለካ፡ የማይቆጠር "ቆይታ" ነው። ከሚሊዮኖች፡ ትሪሊዮኖች፡ ቢሊዮን በላይ ነው።

180 ይህ ግን የጊዜ **አዮኒዮስ** ሲሆን፡ የዘላለም ሕይወት ነው። እና የእንግሊዝኛው ቃሉ ዘላለማዊ ነው። ይህንንም እንደ ዘላለማዊ፡ **አዮኒዮስ**፡ ወይም "ማለቂያ የለሽ ሕይወት" ብለን እናውቀዋለን። አያችሁ? ማለቂያ የሌለው ህይወት ካላችሁ፡ እንዴት ትጠፋላችሁ? የዘላለም አካል ሆናችኋል። ዘላለማዊ የሆነው አንዱ ብቻ ነው።

181 ሰይጣን ዘላለማዊ አይደለም። አይደለም። እሱ—ሰይጣን የሆነ ነው። ሲኦል ዘላለማዊ አይደለም። ሲኦል ተፈጠረ። ዘላለማዊ አይደለም። እነዚህ አካሎችም ዘላለማዊ አይደሉም። የተፈጠሩ ናቸው።

182 የእግዚአብሔር መንፈስ ግን ዘላለማዊ ነው። ጅማሬ አልነበረውም፡ ወይም ፍጻሜ የለውም። ስለዚህ የዘላለም ሕይወትን ማግኘት የምንችልበት ብቸኛው መንገድ፡ በግሪክኛ ቃል፡ **ዞዊ** በመባል የሚታወቀው፡ ትርጉሙም፡ "የእግዚአብሔር የራሱ ሕይወት፡" እንዲህ ነው፡ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች በሆንን ጊዜ የእግዚአብሔር አካል እንሆናለን፡ ያን ጊዜ **አዮኒዮስ** ሕይወት ይኖረናል። ስለዚህ ይህን ቃል የምንገነዘበው፡ እኛ፡ የምንኖረው ክፍል፡ እኛ **ከዚህ እስከዚያ**፡ የምንገነዘበው፡ **አዮኒዮስ** ሕይወት፡ "ማለቂያ የለሽ ሕይወት" ነው። ይህም የእግዚአብሔር የራሱ ሕይወት በእኛ ውስጥ ነው። ኣሜን። ዋው!

183 በቀደም፡ በጉዞ ላይ ሳለሁ፡ ከአንድ የይሖዋ ምሥክር ጋር፡ ተወያይቼ ነበር። እንግዲህ፡ ይህን የምለው የማንንም እምነት ለመናቅ አይደለም። ብዙ የተለወጡ የይሖዋ ምሥክሮች፡ በመካከላችን ተቀምጠዋልና። የቤተክርስቲያናችን ባለአደራ ከሆኑት፡ **አንዱ**፡ ጀሆቫ ዊትነስ ነበር፡ አሁን እርሱ እና ቤተሰቡ ድነዋል። አባቱ አንባቢ ነበር፥ ወንድም ዉድ እና ቤተሰብ ናቸው። አሁን ሁሉም ወንድሞቹ እና እኅቶቹ፣ ሁሉም ከሞላ ጎደል ሁሉም መጥተው መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል፡ ይህም ያደረጉትን ሁሉ በገለጠው በእግዚአብሔር ራእይ ምክንያት ነው። የዚህ ውጤት... አያችሁ? ያሰገኘው ይህ ነው።

184 እንግዲህ፡ እዚህ ጋር፡ ጀሆቫ ዊትነስ መጽሐፍ ውስጥ፡ ይህ የምንተነፍሰው ትንፋሽ ነፍስ እንደሆነ ይናገራል። አሁን፡ ይህ ልክ ሊሆን አይችልም። የምትተነፍሱት ትንፋሽ ነፍስ አይደለም። ጉዳዩ ያ ከሆነ፡ ያንን ነፍስ በመተንፈስህ ምክንያት፡ በ—በአንድ ወቅት የሆነ አይነት ነፍስ ሆነህ፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ ሰው የሆንክ ነህ። ፍጻሜአችሁን ተመልከቱት። እንግዲህ፡ ያንን

የሚተነፍሰው ንፋስ ነው፡ ንፋስ ደግሞ በአፍንጫችሁ በኩል የምትተነፍሱት ነገር ነው።

185 አሁን፡ ይህን ያመጡት ወደ ኋላ መለስ ብለው፡ "እግዚአብሔርም በአፍንጫው እስትንፋስን እፍ አለበት፡ ሕያውም ነፍስ ያለው ሆነ" ከሚለውን ቃል ነው። አሁን፡ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። ሰው የነበረ ከሆነ፡ እግዚአብሔር የሕይወትን ንፋስ ከመንፈሱ በፊት ምን ዓይነት ንፋስ ይተነፍስ ነበር? አያችሁ? ምን ዓይነት ንፋስ ነው? እሱ ሕያውና፡ የሚተነፍስ ሰው ነበር። እሺ፡ እንግዲህ፡ ይህ እንዲህ ከሆነ፡ እንግዲያውስ እያንዳንዱ እንስሳ ሕያው ነፍስ ነው፡ ምክንያቱም የሚተነፍሱት የሰውን ነፍስ፡ ነፍሳችንን፡ እና ሁሉንም ነገር ስለሚተነፍሱ ነው። ኢየሱስም መሞት ባላስፈለገው ነበር። የእንስሳቱ መስዋዕትነት በቂ ይሆን ነበር። አያችሁ? ስለዚህ፡ ወንድሞች ሆይ፡ ይህ ክርክር ውሃ አይቋጥርም።

186 እግዚአብሔር ያደረገው ግን፡ የዘላለምን ሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፡ አሜን፡ ከዚያም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ፡ ሊሞት የማይችል ነፍስ ሆነ። አሁን ተከታተሉኝ። ወደ ማር ውስጥ እንገባለንና፡ እስከ ክርናችሁ ድረስ ጥለቁ። ልብ በሉ። "በአፍንጫው የዘላለም ሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፣ እርሱም የዘላለም ነፍስ ሆነ።" ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር የተነፈሰው፡ ተፈጥሮ የሰራው ሳይሆን፡ እግዚአብሔር ያደረገውን ነው። በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፡ ሕያውም ነፍስ ያለው ሆነ።

እናንተም እንዲህ ትሉኛላችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ አዳም'ኮ ሞቷል።"

187 አስታውሱ፡ አዳም ከመሞቱ በፊት ግን፡ እሱን የዋጀበት በግ ነበረው። ሃሌ ሉያ! "አስቀድሞ ያወቃቸውን፡ ጠራቸው።" ሊቤዣቸውም በግ ወሰደ። ጥላ ነበር፡ አዳም ወደቀ። ከዚያም በጉ ለአዳም ተዘጋጀለት፡ ምክንያቱም አስቀድሞ በአፍንጫው የዘላለም አምላክ እስትንፋስ ተቀብሏል፡ ሕያው ነፍስም ሆኗል። የእግዚአብሔር ልጅ ነበር።

188 ልክ እንደ አፍሪካኛው ቃሉ፡ የራሱ እስትንፋስ አይደለም። አሁን፡ በግሪክኛ ቃሉ አላውቀውም። አፍሪካዊ ቃሉ ግን፡ **ኣሞያህ** በማለት ይጠሩታል፡ ትርጉሙም፡ "ነፋስ፣ የማይታይ ኃይል" ማለት ነው። እንስሳት አሞያህን ይተነፍሳሉ። ኃጢአተኞች አሞያህን ይተነፍሳሉ።

189 በአተነፋፈስ ወደ እኛ የገባ ዘላለማዊ ነፍስ ይህ ከሆነ፡ ታዲያ ስለ ዘለአለማዊ ህይወት ለምን እንታገላለን? ለምንድነው ለዘለአለም ህይወት የምንታገለው? ወንድሞች ሆይ፡ የመልስ ምት አለው። አያችሁ? ይ—ይ— ይህ ሊሆን አይችልም።

190 ነገር ግን፡ እግዚአብሔር፡ በተለይ በአዳም ላይ፡ የዘላለምን ሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፡ እናም ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ አካል ሆነ። እንደ እግዚአብሔር ኃይል ነበረው። ትንሹ አምላክ ነበር። እርሱ የምድር አምላክ ነበር፥ ማለት፡ የሰማይ አምላክ አልነበረም። የምድር አምላክ!

191 አንድ ቀንም የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ገና አማልክት ይሆናሉ። ኢየሱስም እንዲህ አለ፡ "'አማልክት ናችሁ ተብሎ፡ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን'? እንግዲያውስ እግዚአብሔር የጠራቸውን፡ የጎበኛቸውን፡

አማልክት ካላችችኋቸው፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልኩኝ፡ እንዴት እኔን ትኮንኑኛላችሁ? አያችሁ? አሁን ወደ ጠለቀው ነገር እየገባን ነው። አሁን ወደ ታች ዘልቀን ስንወርድ ተከታተሉ።

192 ይኸው፡ እነዚህ ናቸው። አሁን እሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡ ስህተት ግን ሰራ። ስህተት እየሰራ መሆኑን ያውቅ ነበር። አሁን ልብ በሉ፡ አዳም አልተታለለም። መጽሐፍ ቅዱሰም ይመሰክራል። አንደኛ ጢሞቴዎስ 3። "የተታለለው አዳም አይደለም፡ ሴትየዋ ግን በመተላለፍ፡ ተታለለች። አዳም ግን ሚስቱ ስለነበረች፡ ከሔዋን ጋር ሄደ።

193 ልክ እንደ ክርስቶስ፡ እሱ በሰይጣን አልተታለለም፡ ነገር ግን ከሙሽሪቷ ጋር ወደ ሞት ተራመደ። ቤተክርስቲያኗን ይዋጅ ዘንድ፡ ከሙሽራይቱ ጋር ሄደ።

194 አዳም ስህተት እየሰራ መሆኑን፡ በሚገባ እያወቀ ከሄዋን ጋር ተራመደ። አያችሁ? የሚቤዣቸው ጠቦት ግን፡ ተዘጋጅቶላቸው ነበር።

195 ዛሬም፡ ለእነዚህ፡ በእግዚአብሔር አስቀድመው ለታወቁት፡ እና በእግዚአብሔር ለተጠሩት ጠቦቶች፡ ቤዛ አላቸው። "አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። አብም የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።" ልክ ነው? ስለዚህ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ፡ ስማቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ለተጻፈላቸው ሁሉ፡ የተዘጋጀላቸው በግ ነበር። ልክ ለአዳም በግ እንደተዘጋጀለት፡ እያንዳንዳቸውም በትንሣኤ እንዲካፈሉ፡ የጸጋን መንገድ የሚከፍት በግ ተዘጋጅቶላቸው ነበር፡ የአዳም በግ፡ አሁን ልብ በሉ፡ የተዘጋጀ በግ ነበር።

196 እንግዲህ፡ የዛሬዋ ቤተክርስትያን ነች። ቤተ ክርስቲያኒቷ—ማለቴ አይደለም። ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?

197 ይህን የምለው አጉል መንፈሳዊ ለመሆን አይደለም፣ የማንንም ስሜት ለመጉዳትም አይደለም። አስቀድሜ እንደገለጽኩልህ፡ ለዛ አልመጣሁም። እኔ ለመርዳት ነው የመጣሁት፡ ለማድረግ የምሞክረው ነገር ግን...

198 ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በነገራችን ላይ፡ እነዚህ ቸርቾች አብያተ ክርስቲያናት አይደሉም። ቤተ ክርስቲያን አንድ ብቻ ናት። ሌሎች ሁሉ እድሮች ናቸው። አያችሁ? እነዚህ እድሮች ናቸው። ጉዳዬ አይደሉም... ምንም ችግር የለውም። እድሮች መሆናቸው ግን፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ላ—ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ። እንዲያውም፡ የሜቶዲስት እድር፣ የፕሪስባይቴሪያን እድር፣ ወይም የጴንጤቆስጤ እድር አባሎች ናችሁ። አዎን፡ ኧረ-ጉድ ነው። እድሮች! አያችሁ? እንደው በጭራሽ... አያችሁ? አብያተ ክርስቲያናት ተመሳሳይ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች አብረው የሚቀላቀሉባቸው እድሮች ናቸው።

199 ቤተ ክርስቲያን ግን አንድ ብቻ ናት። ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል አይቻልም። በውስጧ ግን ትወለዳላችሁ። በውስጧ ስትወለዱ፡ የራሷ አባል ናችሁ።

200 ልክ እንደ ቤተሰቤ። ለሃምሳ-ሶስት አመታት የብራንሃም ቤተሰብ አባል ሆኛለሁ። ወደዚህ ቤተሰብ እንድቀላቀል ጠይቀውኝ አያውቁም። ለምንድነው?

ወደዚህ ቤተሰብ መቀላቀል አያስፈልገኝም። የተወለድኩት ብራንሃም ሆኜ ነውና።

201 እናንተም በቤተክርስቲያን ተወልዳችሁ። ስለዚህ፡ ሌሎቹ ሁሉ አድሮች ናቸው። ይህን አስባችሁ ታውቃላችሁን? አዎን፡ ወዳጄ።

202 አንድ ቀን ሣር እያጨድኩ ነበር፡ እና እያሰብኩ ነበር፡ እንግዲህ፡ “ታላቋ ቅድስቲቷ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፡” ይሏታል። እንዲሁ እያጨድቁ፡ እየተንቀሳቀስኩ ነበር።

203 እና የሆነ ነገር፡ በኃይል አስቆመኝ እና፡ “እንደዛ ብለህ አትጥራት፡” አለኝ። ዙሪያዬን አየሁ። እንደገና ሣር ማጨድ ጀመርኩ። አሁንም አስቆመኝ፡ እና፡ “እነሱን እንደዚያ ብለህ አትጥራቸው” አለኝ። አክሎም፡ “እንደ ሌሎቹ፡ እነሱም አድር ናቸው። ቤተክርስቲያን አይደሉም። ቤተ ክርስቲያን አንዲት ብቻ ናት።” አያችሁ? እነሱ የአንድ አድር አባላት ናቸው፡ ምክንያቱም የምትቀላቀሉት ነገር አድር ነው። ቤተክርስቲያንን ግን መቀላቀል አይቻልም። ቤተክርስቲያን፡ የምትወለዱበት ነው። በአዲሱ ልደት አባላት ትሆናላችሁ፡ ከዚያም የቤተሰብ አባል፡ ወንድም ወይም እህት እንሆናለን።

204 እስኪ አሁን ከዚህ **ዘ እምፋቲክ ዲያግሎት**፡ እዚህ ላይ፡ ከራእይ 17፡ 3 እና፣ ከ **ዘ እምፋቲክ ዲያግሎት** አፖካሊፕስ ላንብብላችሁ። እና ምን እንደሚል፡ እንዴት እንደሚነበብ፡ እ—እንዴት በሚያስደንቅ ሁኔታ እንደሚሰማማ ተመልከቱ። ራዕይ 16፣ 17። በጣም ጥሩ። አሁን፡ ከዚህ እናንብብ፡ ለአፍታ ብቻ። ይህን፡ በደንብ አድምጡ፡ ራእይ 17፡3።

> **እናም ከእነዚያ ከሰባቱ መላእክት አንዱ**... **ሰባት ጽዋዎች የያዘው መጥቶ ተናገረኝ፡...**

205 ይህን **ከመዝገበ ቃላት**፡ እያነበብኩላችሁ ነው። “ና... ”

> ... **“ና፡ በብዙ ውሃ ላይ** የተቀመጠችውን፡ **የዚችን ታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ፥**

206 ቫቲካን እንደሆነች ሁላችንም እናውቃለን። እዚህ ጋር በካቶሊክ ቤተክርስቲያን የሚታተም፡ **አወር ሰንደይ ቪዚተር**፡ የሆነውን ሁሉ በትክክል ይነግረናል። አያችሁ?

207 ለዚያም ምላሽ ሲሰጥ፡ “እስኪ አንዴ ቆይ፡” አለኝ። እሱም፡ “ስድስት መቶ ስልሳ-ስድስት ሊሆኑ የሚችሉ፡” ብዙ ዓይነት ስሞች ነበሩ፡” አለኝ።

እኔም፡ “ግን አንዴ ቆይ” አልኩት።

አለኝም፡ “ምናልባት ስምህም ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ሊሆን ይችላል... ”

208 “ግን” “እንግዲህ፡ አየህ፡ እኔ ዓለምን እየገዛሁ፡ በሰባት ተራሮች ላይ አልቀመጥም፡” አልኩት። ኧሃ-ሃህ! አየህ? ልክ ነው። አያችሁ?

209 [ወንድም ብራንሃም ራእይ 17:1ን ከ **ዘ እምፋቲክ ዲያግሎት** ውስጥ አነበበ—አርታዒ።]

> ... **በብዙ ውሃ** ላይ **የተቀመጠችውን**፡ **የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ ያሳየሃለሁ፥**

210 ውኆች፡ ራእይ 17፡15 ላይ፡ "ወገኖች እና የሕዝብ ብዛትና" ናቸው ይለዋል። አያችሁ?

**የምድር ነገሥታት ከእርሰዋ ጋር** ሴሰኑ፥ **በምድር የሚኖሩም ከዝሙትዋ**... **ወይን ጠጅ** ሰከሩ።

211 ከዚያስ ምን?

**እናም** በ**መንፈስ፡ ወደ በረሃ፡ መራኝ፥...**

212 ይህ **ዘ ኢምፋቲክ ዲያግሎት** ነው። አያችሁ?

**... እና አንዲት ሴት አስቀያሚ ሰዎች በተሞላ፡ በቀይ** ቀለም **አውሬ** ላይ **ተቀምጣ አየሁ፡...**

213 አሁን፡ ኪንግ ጄምስ፡ "የሰድብ ሰዎች የሞሉበት፡" ይለዋል። እስኪ አንድ አፍታ፡ ከአፍታ በኋላ፡ እመለስበታለሁ። ራእይ፡ 3 ላይ። ይኸው፡ እንዲህ ይላል። እሺ። ራእይ፡ 17 ማለቴ ነው፡ 7 ሳይሆን፡ 17፣ 3ኛውን ቁጥር አዳምጡ።

**በመንፈስ**ም **ወደ በረሃ ወሰደኝ። የሰድብ**ም **ሰዎች በሞላበት፡ በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት** ተቀምጣ **አየሁ፡...**

214 እንግሊዘኛም እንዲህ ያስቀምጠዋል። የመጀመሪያው የግሪክ ቅጂ **ዘ ዲያግሎት** ግን ይህን ይመስላል፡ ራዕይ 17፡3። አዳምጡ።

በመንፈስም፡ ወደ ምድረ በዳ፡ መራኝ፥ **እና አንዲት ሴት በተሰደቡ ሰዎች በተሞላ፡ በቀይ** ቀለም **አውሬ—አውሬ** ላይ፡ **ተቀምጣ አየሁ፡...**

215 "በሰድብ ሰዎች" እና "የተሰደቡ ሰዎች" መካከል፡ ትልቅ ልዩነት አለ። ምንድነው? እኛ... እንግዲህ፡ እሷ፡

**... የጋለሞታዎች እናት...**

216 ሁላችንም እናውቀዋለን። ግን ምንድን ነው? [አንድ ሰው፡ "የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን" አለ።—አርታዒ።] እንግዲህ ሌላ አይጠበቅባችሁም... አዎን፡ ልክ ነው፡ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርቲያን ናት። ነገር ግን "በብዙ የተሰደቡ ሰዎች" የተሞላች ናት፡ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን፣ ሉተራን፣ እራሳቸውን፡ "የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት።" የተሰደቡ ሰዎች! "በሰድብ ሰዎች" እና "በተሰደቡ ሰዎች" መካከል ሰፊ ልዩነት አለ። እራሳቸውን፡ "የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን" ብለው በመጥራት፡ በዓለም ፊት እራሳቸውን በራሳቸው ይወክላሉ፥ የካርታ ድግሶች፡ መጠጥ፡ አሸንክታብ፡ የሾርባ እራት፡ እና ሌላ ሁሉ፡ እያደረጉ ይቀጥላሉ።

217 ቤተ ክርስቲያን አንድ ብቻ ናት። በውስጧም ትወለዳላችሁ። በበጉ ደም እስክታጠቡ ድረስ እና በመንፈስ ቅዱስ እስክታተሙ ድረስ ወደ ውስጥ አትገቡም።

218 "በሰድብ ሰዎች" እና "የተሰደቡ ሰዎች" መካከል በጣም ልዩነት አለ። ገባችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

219 ዛሬ ጠዋት እዚህ እየመጣሁ ሳነበው፡ ይህ... ገባኝ፡ የሆነ ነገር፡ "ቢሮህ ግባና። **ዘ ዲያግሎትን** ያዝ" አለኝ።

220 እንግዲህ፡ መታዘዝ ብቻ ነው። በቃ። ገባሁ። ራዕይ 17ን ከፈትኩ። "ይህን እንዳነብ ለምን ፈለግከኝ፡" አልኩትና? ማንበብ ጀመርኩ። [ወንድም ብራንሃም ጣቶቹን አንቃጨለ—አርታዒ።] ልክ እንደገባሁበት፡ "ይኸው ደረስኩበት።" እርሳስ አንሥቼ ጻፍኩት። "ይኸው ደረስኩበት፡" አልኩኝ።

221 እንግዲህ፡ ድርጅቶችን ይወርፋል በማለት በእኔ ላይ ያጉረመርማሉ። በእነዚያ የተሰደቡ ሰሞች፡ እራሳቸውን ይጠራሉ፡ "የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት፣ የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያን፡ የሜቶዲስት አብያተ ክርስቲያናት፣ እና አብያተ ክርስቲያናት።" እድሮች እንጂ፡ አብያተ ክርስቲያናት አይደሉም።

222 አንዲት ቤተክርስቲያን ብቻ አለች፡ ያውም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ናት። እና ምንድነው? አሁን በምድር እየሰራች ያለች ምስጢራዊትዋ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል፡ የክርስቶስ አካል ብልቶች ለመሆን፡ ከእነዚያ ሁሉ ማሕበራት የተውጣጡ ብልቶች ናቸው። በውስጧ መወለድ እንጂ፡ ወደሷ መቀላቀል አይገባችሁም።

223 ወደሷ መቀላቀል ደግሞ፡ ይህች ሴት፡ የተሰደበ ስም አላት። ይህች ሴት፡ ሰልጣኗ!

224 አሁንም የሚያደርጉትን ተመልከቷቸው ስለ ሀይማኖት ተራ ሀሳብ ያላቸውን ሁሉ ወሰደው፡ ወደ አላስካ ሊልኩ እያሰቡ ነው። ይህን አይታችኋል። እንግዳ እምነቶቻችን ሁሉ።

225 ይህ ምንድን ነው? የዓለም አብያተ ክርስቲያናት፡ ካውንስል ካቶሊኮች አሁን ትልቅ-ስብሰባቸውን አሁን እየሞከሩት ባሉት፡ በዚያ፡ በቫቲካን እያደረጉ ነው። እነዚህ ሁሉ ጳጳሳት፡ እና ሌሎቹ፡ ኮሚኒዝምን ለመዋጋት፡ እየተግባቡ ይገኛሉ። ዓለም ኮሚኒዝምን እየተዋጋ ነው፡ ብቸኛው ሊያደርጉት የሚችሉት ካቶሊክን መቀላቀል ብቻ ነው።

226 ዛሬም እንደዛ ነው። እነሆ እኛ፡ እንዳልኩትም፡ ወደ ኪሳራ... ልንከሰር ተቃርበናል። አሁን የዛሬ አስራ አራት አመት የሚከፈል ገንዘብ፡ እየተበደርን፡ በግብር ጉዳዮች ላይ እየፈጀነው እንገኛለን። ይሄን ያህል ሄደናል። የዓለምን ገንዘብ የያዘው ማነው? የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን። ለዩናይትድ ስቴትስ የምታበድራት እንዴት ነው? እነዚህን የትምባሆ እና የውስኪ ኩባንያዎች እና ሌሎችን ለማቆየት። በእርግጥ፡ ከእነሱ ይበደራሉ። ይህን ሲያደርጉ፡ ብኩርናቸውን፡ በቀጥታ፡ ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይሸጣሉ። አንድ ነገ። ይህንን ልብ በሉ፡ ጋዜጣ ከማንበብ በበለጠ ግልጽ፡ ግልጽ ነው። ይኸው ነው። አያችሁ?

227 እራሳቸውን፡ "የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን" ብለው የሚጠሩ፡ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን እና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ካቶሊኮች እና መሰሎቻቸው በሙሉ የተሰደበ ሰም ያለው ይህ የአውሬው ሰልጣን ነው። እራሳችሁን "እንዲህ ነኝ... " ትላላችሁ፡ ተናግሬአለሁ...

228 በቅርብ ጊዜ፡ ለአንድ ሰው ለመጸለይ፡ ሆስፒታሉ ጋር ሄጄ ነበር። ለእናንቴ ነበርና፡ እኔም "እንጸልያለን... " አልኳት። "ለእናቴ ጸሎት ልናደርግላት ነው፡" አልኳት።

ሴትየዋም፡ "መጋረጃውን ሳበው" አለች።

እኔም፡ “ክርስቲያን አይደለሽም’ዴ” አልኳት?

እሷም፡ “እኛ ሜቶዲስቶች ነን” አለችኝ።

229 እኔም፡ “አመሰግናለው። ምናልባት አማኝ ነሽ ብዬ አሰቤ ነው።” መጋረጃውን በዙሪያዬ ሳብኩት። አየሽ? ስለዚህ፡ ክርስቲያን ካልሆንሽ፡ ሌላ ነገር ነሽ። አየሽ?

230 እኛ ግን፡ “ሜቶዲስቶች ነን፡” ይህ ስድብ ነው። አውሬው፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ አብያተ ክርስቲያናት የምንላቸው፡ አብያተ ክርስቲያናት አይደሉም። ይህ በትክክል መቀዳቱን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ። አዎን። አብያተ ክርስቲያናት አይደሉም። እነዚህ እድሮች ናቸው። ሰዎች የሚቀላቀሏቸው ናቸው።

231 የሕያው እግዚአብሔር ቤት ክርስቲያንን ግን መቀላቀል አትችሉም። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ በውስጧ ትወለዳላችሁ። በመንፈስ ቅዱስም ስትጠመቁ፡ እነዚህ ቁመናዎች በእናንተ ውስጥ፡ በመንፈስ ቅዱስ ይታተማሉ፡ ስለዚህም “ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን አያደርግም።” “አይቻለውም።” ያ ነው። አቤት፡ አቤት!

ስለዚህ ጉዳይ ቀኑን ሙሉ ማውራት እንችላለን፡ አይደል?

232 ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር እስትንፋስ የተወለደች ምስጢራዊ የክርስቶስ አካል ነች። ኡፍፍፍ! ገባችሁ ወይ? [ጉባኤው “አሜን” አለ።—አርታዒ።] የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር እስትንፋስ ተወለደች። በመንፈሳዊ አገላለጽ፡ እግዚአብሔር በአዳም በአፍንጫው፡ እስትንፋሱን እፍ አለበትና፡ ሕያው ነፍስ ሆነ። ጴንጤዎች፡ ወይም እውነተኛዋ የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን፡ ከእግዚአብሔር እስትንፋስ እንደተወለደች ታውቃላችሁን?

233 በዛ ላይ ትንሽ ጊዜ ወስጄ፡ አንድ ነገር ላንብብላችሁ። እስቲ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ ልየው። እኔ የፈለግኩት፡ ቅዱስ ዮሐንስ፡ ይመስለኛል። የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እንደዚያ መሆን አለመሆኗን፡ እናያለን። ቅዱስ ዮሐንስ፡ እንመልከት፡ ከ16፣ 19፥20 ይመስለኛል። እሺ። እዚህ ጋር፡ የምናገኘው ይመስለኛል። በጣም ጥሩ። ላንብብላችሁና፡ በመጀመሪያ በአዳም ላይ እንደሆነ፡ ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር እስትንፋስ፡ መወለድ አለመወለዷን እናያለን። ተከታተሉ።

> ያም **ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተኛው፡ በመሸ ጊዜ፡ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት አይሁድን** ስለ **ፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ፥** ኢየሱስ መጣና **በመካከላ**ቸውም **ቆሞ፡ ሰላም ለእናንተ ይሁን፡ አላቸው።**
>
> **ይህንም ብሎ፡ እጆቹንም ጎኑንም...** አሳያቸው። ያን ጊዜ... **ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ፡ ደስ አላቸው።** ኢየሱስም...
>
> **ኢየሱስም ዳግመኛ፡ ሰላም ለእናንተ ይሁን፥ አብ እንደ** ላከኝ፡... **እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው።**

234 ልብ በሉ። የላከው አብ እርሱ በእርሱ ነበረ። ኢየሱስም ደቀ መዝሙርን በላከ ጊዜ፡ በእርሱ ውስጥ በዚያ አለ። እርሱን የላከው፡ እግዚአብሔር ራሱ።

**ይህንም ብሎ፡ እፍ አለባቸው፡ እና... መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ** አላቸው፥

235 ከእግዚአብሔር እስትንፋስ የተወለደች፡ ቤተ ክርስቲያን! በዚህ ሁኔታ፡ ይህ ቁመና በዚያ በውስጣቸው ሆኖ ቅርጽ በያዘ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር እስትንፋስ በላያቸው ላይ ነፈስ፡ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡" ያን ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ። የፈለግከውን አይነት ወገን ብትቀላቀልም፡ በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ በእግዚአብሔር እስትንፋስ ተወልደሃል። እግዚአብሔርም እፍ አለባቸውና፡ እንዲህም አላቸው፡ "መንፈስ ቅዱስን፡" አቤት፡ "ተቀበሉ።" ኦህ፡ ማይ! ይኸው ነው።

236 "ናና ተቀላቀል፡ ስምህን አስመዝግብ፡" አይደለም። እስከነ ሾርባ እራታችሁ እና ልዩ ልዩ ነገሮቻችሁ፡ እድራችሁን ትቀላቀላላችሁ። የሜቶዲስት እድር፣ የባፕቲስት እድር፣ የፕሪስባይቴሪያን እድር፣ የካቶሊክ እድር፣ ወይም የጴንጤቆስጤ እድር፣ መቀላቀል የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር መቀላቀል ትችላላችሁ፣ ቢሆንም እድርን ትቀላቀላላችሁ።

237 የእግዚአብሔር ልጅ ከሆናችሁ ግን፡ የተወለዳችሁት ከእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። ኣሜን። አሁን በዚህ ጉዳይ ላይ ከዚህ ባላልፍ ይሻላል። እሺ።

238 የእግዚአብሔር ሕይወት በእናንተ ውስጥ አለ፡ ኢየሱስ ተናግሯል። አንድ ደቂቃ ብቻ። ኢየሱስም፡ "እኔ የወይን ግንድ ነኝ። እናንተ ቅርንጫፍ ናችሁ።"

239 አሁን ተመልከቱ። በኢየሱስ ላይ ለምን አጉረመረሙ? በኢየሱስ ላይ እንዲያጉረመርሙ ያደረጋቸው፡ እርሱ ሰው ሲሆን ራሱን አምላክ ስላደረገ ነው። አምላክ ነበር። እግዚአብሔር በክርስቶስ ነበር። አያችሁ? እንዲሁም አላቸው። እንዲህ ይላቸው ነበር፡ "እኔን አትዩ። እኔ አይደለሁም፡ አባቴ ነው፡ እርሱም በእኔ ይኖራል።" ኦህ! አያችሁ?

240 እነርሱ፡ ከማርያም ዘንድ የተወለደውን ያ ታናሽ ሥጋው ተመለከቱ። አያችሁ? ያ እግዚአብሔር አልነበረም። ያ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን በዚያ አካል ውስጥ ነበር። እግዚአብሔር ነበር። እንዲህም አለ፡ "የአባቴን ሥራ ባላደርግ፡ እንግዲያውስ ውቀሱኝ። ነገር ግን ከእናንተ በኃጢአት፣ በቃሉ ባለማመን የሚወቅሰኝ ማን ነው? በእግዚአብሔር የተነገረው ቃል በእኔ ዘንድ ያልተፈጸመ የቱ ነው? ኃጢአት አለማመን ነው። "ከእናንተ ኃጢአት ሠርተሃል ብሎ የሚወቅሰኝ ማን ነው? " ኃጢአት አለማመን ነው። "አሳዩኝ። የአባቴን ሥራ ባላደርግ፡ አትመኑኝ። ነገር ግን ሥራውን ባደርግ ግን... እኔን ባታምኑኝ እንኳ፣ እኔ የማደርገውን ሥራ እመኑ፤ የሚመሰክሩት እነርሱ ናቸውና። በሌላ አነጋገር፡ "አብ በእኔ ውስጥ ነው፤ እርሱ ስለ ራሱ ይመሰክራል።" ምክንያቱም፡ "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ፡ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር። ገባችሁ? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—እርታዒ።]

241 እንግዲህ፡ አሁን፡ በወይኑ ግንድ ውስጥ ያለው ያው ህይወት በቅርንጫፍ ውስጥ አለ። እንዴት ነው የምትቀላቀለው? አይቻልም።

242 በአንድ ወቅት፡ በአሪዞና ውስጥ በወንድም ሻሪት ጓሮ ውስጥ አንድ ዛፍ አይቻለሁ፡ ዘጠኝ የተለያዩ የሆምጣጤ ፍራፍሬዎች ነበሩት። ምን ነበር? የ— የብርቱካን ዛፍ፡ የናቬል ብርቱካን ዛፍ ነበር። በላዩ ላይ ግን ሎ—ሎ—ሎሚ፣ መንደሪን፣ ታንጀሎ፣ እና የወይን ፍሬ ነበረው። ልዩ ልዩ ነበር። በዚያ ቆሜ፡

ያንን ዛፍ አየሁት። እኔም፡ “ወንድም ሻሪት፡ ይህ ዛፍ የብርቱካን ዛፍ ነው ነው የምትለኝ” አልኩት?

እርሱም “አዎን፡” አለኝ።

243 እኔም፡ “እሺ፣ እንዴት? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ” አልኩትም፡ “**እዚህ** ጋር የወይን ፍሬ ይታየኛል፡ እዚህ ጋር መንደሪን፡ **እዚህ** ጋር ታንጄሎ፡ ሎሚም **እዚህ** ጋር፡ ሌሎች ፍራፍሬዎች ጭምር። ይህ እንዴት ይሆናል? ”

እሱም “አዎን፡ አየህ፡ እነዚህ የተዳቀሉ ናቸው፡” አለኝ።

244 “ኦህ!” እኔም፡ “እሺ፣ አንድ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። እስኪ፡ ያን ወይን ፍሬ እና ሎሚ ልቀመው። እሺ፡ በሚቀጥለው ዓመት፡ ምን ይሆናል? ብርቱካን በእርግጠኝነት ከውስጡ ያፈራል።”

“በፍፁም፡ አይደለም፡” አለኝ። “ሎሚ ከውስጡ ያፈራል። አየህ? ”

“ኦህ” አልኩት፡ “አመሰግናለሁ” አልኩት። አያችሁ?

ያንን ማድረግ አይቻላችሁም። መቀላቀል አትችሉም።

245 “ነገር ግን፡” “ዛፉ ራሱ አመት በጨመረ ቁጥር እና አዲስ ቅርንጫፍ ባወጣ ቁጥር፡ ብርቱካን ያፈራል፡ ወይኑም የራሱ ቅርንጫፍ ቢያወጣም።”

246 እኛም ለማድረግ የሞከርነው የሱ አባላት መሆን ነው፡ የምንኖረውም በክርስትና ስም ስር ነው። ምክንያቱም፡ እኛ፡ በተለምዶ አባባል፡ የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ሆምጣጣ ፍሬ ነን።

247 ነገር ግን የወይን ግንዱ ራሱ ሌላ ወይን ግንድ ቢያፈራ፡ እንደ መጀመሪያው ወይን ይሆናል። በመጀመሪያ ያፈራውን የወይን ግንድ ተከትሎ፡ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከተጻፈ፥ ከዚህ ሌላ ቢያወጣ፡ ከጀርባው ሌላ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይጻፋል። ትክክል ነው።

248 ስለዚህ፡ እድሮች ብቻ እየተቀላቀላችሁ ነው። ከወይኑ ከተወለዳችሁ ግን... ፍሬ ይኖራችኋል። በትክክል። ፍሬ ይኖራችኋል፡ እናንተ ግን ምን አደረጋችሁ? “የአምልኮት መልክ አላችሁ፡ ኃይሉን ግን ክዳችኋል።” ምልክቶችን ትክዳላችሁ። ድንቆችን ትክዳላችሁ። መንፈስ ቅዱስን ትክዳላችሁ። በልሳን መናገር ትክዳላችሁ። ራእዮቹን ትክዳላችሁ። ትንቢቶቹን ትክዳላችሁ። ፈውስ ትክዳላችሁ። በዚህ ሁሉ፡ ግን፡ “ለራሳችሁ ስም ትሰጣላችሁ።” መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ማለቱ አያስደንቅም፡ “በተሰደቡ ሰሞች የተሞሉ፡ የሰዎች ስብሰብ፣ ኃይል፣ አዎን፡ ራሳቸውን ‘ክርስቲያኖች’ ብለው የሚጠሩ።” “የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል። እንደነዚህ ካሉት ሰዎች ራቁ፤ ምክንያቱም ከመካከላቸው ደካሞችና አእምሮአቸው የጐደላቸውና ልዩ ልዩ ዓይነት ምኞት ያለባቸውን ሴቶች የሚመሩ አንዳንዶች አሉና።”

249 ልዩ ልዩ ዓይነት ድርጅቶች! ቤተ ክርስቲያን **በዚህ** ዓይነት ማኅበረሰብና፣ **በዚያ** ዓይነት ማኅበረሰብ የተሞላች ናት። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበረሰብስ? አያችሁ? እነዚህ ሁሉ ነገሮች አሉን፣ እና ቤተ ክርስቲያንን ከልክ በላይ ተሸክማለች። ይኸው እንግዲህ።

መቼም ቤተክርስቲያን መቀላቀል አትችሉም።

250 የተቀላቀላችሁት እድር ነው። የአንድ እድር አባላት ናችሁ፣ የሰዎች ስብሰብ፣ ልክ እንደ እድር ነው። "**ይህን** እናምናለን። የራሳችን ስርዓቶች አሉን። የራሳችን ሚስጥሮች፡ ወዘተረፈ አሉን። ተመሳሳይ ነገር ታደርጋላችሁ፡ ቤተ ክርስቲያን-ተብዬ ትገባላችሁ።

251 ቤተክርስቲያንን መቀላቀል ግን አትችሉም። የእድር ማሕበር እንጂ፡ ቤተክርስቲያን አልተቀላቀላችሁም፡ምክንያቱም ወደዚህ ቤተክርስቲያን እና ወደ ወይኑ መግቢያው በመወለድ ነው።

252 አሁን ለአፍታ ብቻ። አስተውሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እጨርሳለሁ። ልብ በሉ። ይቅርታ። ይህን ማለቴ አ—አልነበረም። አስተውሉ። ተመልከቱ።

253 እግዚአብሔር ይህች ሙሽራ በዚያ መንፈስ ካጠናከራት፣ ከዚያም ግለሰቡን ከዚያ ከመንፈሱ ጋር ያጠናክረዋል፣ አያችሁ፡ ያን ጊዜ በዚያ መንግስት ትወለዳላችሁ። ስለዚህ **በዚህች** ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረው ያው ህይወት፡ **በዚያች** ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ **በዚያች፣ በዚያች፣ በዚያች፣ በዚያች** ነው። በእቅፉ ውስጥ የነበረው ያው ሕይወት፣ ወይኑ፣ ኢየሱስ፣ ባፈራው አባል ውስጥ ይኖራል። ክብር! "እንግዲህ እኔ የማደርገውን የማደርገውን ሥራ፡ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" ትክክለኛው የክርስቶስ አካል አባል ይህ ነው፡ በሱ ዘንድ የተጣበቀበት ሌላ ነገር የለውም። የዚህ ግለሰብ ሥራ ራሱ ከየት እንደመጣ ያረጋግጣል። ህይወቱ ስለምንነቱ ይመሰክራል።

254 "የምን አባል ነህ? የየትኛው አካል አባል ነህ? " የክርስቶስ አካል። "እሺ፡ የት ነው የተቀላቀልከው? " አልተቀላቀልኩም። በውስጧ ተወለድኩ። አየህ? በውስጧ ተወለድኩ።

255 እነሱን መንገር አያስፈልግም። ምን እንደተፈጠረ ያውቃሉ። "እናንተ፡ መብራት አብርታችሁ በላዩ ላይ ባልዲ ማድረግ እንዴት ይቻላችኋል? " አላቸው። አያችሁ? አይ፡ አይደረግም።

256 ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስትወለዱ፡ ሕይወታችሁ፡ በኢየሱስ የነበረው ሕይወት ይሆናል። ስለዚህ የነፍሣች ጥማት ያድርባችኋል። ያን ጊዜ ሰዎች ወደ መሠዊያው እንዲመጡ መለመን፡ አይጠበቅባችሁም። መጥቶ በመሠዊያው ካሉት ጋር እንዲቀላቀል፡ ማንንም መለመን አያስፈልጋችሁም። አዎን። በውስጣችሁ ስለታተመ፡ ነ—ነ—ነ—ነገሮች ወዲያውኑ ይንቀሳቀሳሉ። የእግዚአብሔር ብልቶች ናችሁ። በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋል።

አሁንስ "መንፈስ ቅዱስ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ አውቃችኋልን?

257 "ዘልዬአለሁ፣ ጮኬአለሁ፣ የሆነ ስሜት ይሰማኛል፡" አይሰራም። እነዚህም ይኑሩ። ዘልዬአለሁ፣ ጮኬአለሁ፣ ልዩ ስሜት ይሰማኛል። "በልሳኖች ተናገሬአለሁ።" አዎን መንፈስ ቅዱስ በልሳኖች እንደሚናገር አምናለሁ። በትክክል። "ተርጉሜአለሁ።" አዎን፡ ወዳጄ። ይህ መሆኑም፡ አምናለሁ። ዋናው ነገሩ ግን ያ አይደለም። እኔ የምናገረው ስለዚያ አይደለም። እዚህ የሆነ ቦታ የሚያፈስ ነገር ሊኖርባችሁ ይችላል። **በዚህ** በትዕግስታችሁ ውስጥ፡ የሚያፈስ ነገር ሊኖር ይችላል።

258 ሰው ፊትህን፡ በአንዱ በኩል ቢመታህ፡ ሌላኛው ጎን ታዞራለህን? አንተ ግን፡ "ያ ርኩስ ግብዝ" ትለዋለህ! ስለዚህ፡ የሆነ ቦታ፡ መፍሰስ አለ። ያንን ወደ ጎን ብንተወው ይሻለናል። እሺ። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ግን አውቃችኋል።

259 በክርስቶስ አካል ስትታተሙ ግን፡ ያን ጊዜ በመንፈስ-ትሞላላችሁ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ትሆናላችሁ።

260 ኦህ፡ የሆነ ነገር ለማንበብ አስር ተጨማሪ ደቂቃ፡ አንድ ነገር ለማንበብ ብትሰጡኝ እመኛለሁ። [ጉባኤው "ቀጥል። አንብብ፡ ወንድማችን፡" አለው።—አርታዒ።] አስር ደቂቃ ትታገሱኛላችሁ? ["አዎን።"] የሆነ ነገር ማንበብ እፈልጋለሁ፡ ትንሽ ብቻ። እውነቱን ለመናገር፡ ግድ የላችሁም፡ ባቄላው አያርም። ለጥቂጥ ደቂቃዎች ብቻ ይሄን ብናነበው፡ እሺ፡ ቃል እገባላችኋለሁ። በጣም ጥሩ ነው ይሄን ማለፍ አልችልም። መናገር የምፈልጋቸው፡ ወደ አእምሮዬ የሚመጡ፡ ሁለት ነገሮች አሉ።

261 ስለ ዘላለም ሕይወት የሚናገረውን፡ ዮሐንስ ምዕራፍ 3ን፡ እንውሰድ። የዘላለም ሕይወት ጉዳይ፡ የእግዚአብሔርን ሕይወት በተመለከተ ትንሽ እንመልከት። አሁን፡ አሁን በደንብ ተመልከቱ።

> **ከፈሪሳውያንም ወገን፡ የአይሁድ አለቃ የሆነ፡ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፥**
>
> እርሱም **በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ፡ አለው፡ መምህር ሆይ፡ አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ መምህር መሆንህን እናውቃለን፥... እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ካልሆነ በቀር... ማንም ሰው እነዚህን ተአምራት ሊያደርግ አይችልም።**

262 ስለዚህ፡ እነርሱ፡ የሳንሄድሪን አለቆች፡ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አወቁ። ያውቁታል። ይህ አለቃቸውም፡ እንዲህ ይለዋል፡ "አንተ ከእግዚአብሔር የመጣህ መምህር እንደ ሆንህ እናውቃለን፡ የእግዚአብሔር የራሱ ሕይወት በአንተ ይፈስሳልና።" አያችሁ? "ትምህርትህ ያንተ እንዳልሆነ እናውቃለን። የእግዚአብሔር ነው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር እያረጋገጠው ነው።" አያችሁ? "የእግዚአብሔር ሕይወት በአንተ ውስጥ ይፈስሳል።" አሁን በደንብ ተመልከቱ።

> **ኢየሱስም መልሶ፡ እውነት፡... እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም።**

263 ኦህ፡ ማይ! "ቤተክርስቲያኔን ካልቀላቀልክ በቀር"? ኦህ! እንዴት እንደሚስቱት አይታችኋል? አያችሁ? አያችሁ?

> ኢየሱስም፡ መልሶ፡ **እውነት፣ እውነት፣ እልሃለሁ፡ ሰው ከውኃና... ከመንፈስ፡ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።**
>
> **ከስጋ የተወለደ... ስጋ ነው፥ ከመንፈስ የተወለደ... መንፈስ ነው።**
>
> **ዳግመኛ ልትወለዱ፡ ያስፈልጋችኋል ስላልኋችሁ አታድንቁ።**

**ነፋሱ ወደሚወደው** ይነፍሳል፡... አየህ፡ እንደገናም ይመለሣል፡ አየህ፡ ይመለሳል፡ አየህ።

**ነፋሱ ወደሚወደው** ይነፍሳል፡... **ድምፁን አትሰ**ማውም... **ድምፁን መስማት** ትችላለህ፡ **ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ፡ ወዴትም እንደሚሄድ ማወቅ አትችልም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሰውም... እንዲሁ ነው።**

**ኒቆዲሞስ መልሶ፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?**

**ኢየሱስም መልሶ። አንተ የእስራኤል መምህር ሆነህ፡ ይህን** አታውቅምን?

264 ወንድሜ፡ ይኸው ተመልከታቸው፡ አ—አ D.D.፣ Ph.D.፣ ድርብ-L.D.፣ አየህ፡ "ይህን አታውቅምን?"

**በእውነት፣... እልሃለሁ፥ የምናውቀውን እንናገራለን፥ ያየነውም እንመሰክራለን፥ እናንተም ምስክሮቻችንን አትቀበሉም።**

265 "እነዚህን ነገሮች እናውቃለን። አይተነዋል። እናውቀዋለን፣ ምስክሮቻችንን እንኳን አትቀበሉም።" የቤተክርስቲያን-አባላት! አያችሁ?

**ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ፡ ካላመናችሁ፡ ሰማያዊ ነገሮች; ብነግራችሁ... እንዴት ታምናላችሁ?**

266 አሁን ይህን አዳምጡ። ተመልከቱ።

**ከሰማይም** ከ**ወረደው በቀር፡ ወደ ሰማይ** የወጣ **ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።**

267 እስኪ አስቡት።

268 ታውቃላችሁ፡ በአንድ ወቅት፡ እንዲህ አለ፡ "ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?"

"የዳዊት ልጅ፡" አሉ።

269 እርሱም፡ "ለምን ታዲያ ዳዊት፡ በመንፈስ፡ እንዲህ አለው፡ 'ጌታ ጌታዬን፡ "በቀኜ ተቀመጥ'"? እንዴት ጌታ እና ልጁ ሊሆን ይችላል?" ማንም ጥያቄ አላቀረበለትም።

270 በራዕይ ላይ፡ እንዲህ አለ። "እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ።" አያችሁ? "እኔ ወይንና ቅርንጫፍ ነኝ። መጀመሪያ ነኝ። ከመጀመሪያው በፊት ነበርኩ። መጀመሪያ ነበርኩ እ—እኔም፡ የርሱ ዘር ነበርኩ።"

271 አሁን፡ እዚህ ላይ እንዲህ አለ፡ "አሁን በሰማይ ካለው የሰው ልጅ በቀር ማንም ከሰማይ የወረደ የለም።"

272 በአንድ ወቅት፡ አንዲት ሴት፡ ጠየቀችኝ። እኔም "ይሄን መልሺልኝ፡" አልኳት።

አልኳትም፡ "ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ወደ ማን ጸለየ?"

273 እንዲህ አልኳት፡ "ይህ የተናገረው ስለ ማን ነበር፡ ''ከሰማይ ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፡ አሁን በሰማይ ያለው... የሰው ልጅ ነው እንጂ'? ማን?"

274 እነሆ፥ በዚህ በሰገነት ላይ ቆሞ፡ ከኒቆዲሞስ ጋር እየተናገረ “እኔ በሰማይ ውስጥ ነኝ” አለው። ልክ ነው? ይህን እስከ ዛሬ ማታ ድረስ እናቆየው። ምን ትላላችሁ? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] እጅግ ረፍዷል። ኦህ፡ ማይ! ዛሬ እስከ ከሰዓት ድረስ፡ ይሄን እስላስሉት።

275 ወደ ቤተክርስቲያን እንዴት ትገባላችሁ? [ጉባኤው፡ “በመወለድ” አሉ።—አርታዒ።] በመወለድ። በምን? በእግዚአብሔር እስትንፋስ።

ተንፍስብኝ፡ ተንፍስብኝ፡
የሕያው አምላክ መንፈስ ሆይ፡ ተንፍስብኝ።

276 ጸሎቴ ይህ ነው፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ይንፈስ። ኦህ፡ ማይ! ምክንያቱም፡ የእግዚአብሔር እስትንፋስ፡ ምንድነው? በእግዚአብሔር መንግሥት የታተመ፥ በመጀመሪያ ምስክሬን ሰናገር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አምን እንደነበር፡ አውቃለሁ። አዎን።

ከዚያም በእምነቴ ላይ በጎነትን፡ አምላካዊ በጎነትን፡ እጨምራለሁ።

በበጎነቴም፡ የቃል እውቀትን እጨምራለሁ።

277 በእውቀቴ ላይ፡ ራስ መግዛትን፡ ራስ-መቆጣጠርን እጨምራለሁ። “አገሬ ሆይ፡ ከዳር እስከ ዳር፡ ነፍሴን ራስ-በመግዛት የምትሸልሚኝ አንቺ ነሽ።” የሚለውን እወደዋለሁ። አያችሁ?

278 ትዕግስት። ኦህ፡ ማይ! የተፈተኑ። አትጨነቁ፥ ሰይጣን እነሱን ይቆጥርላችኋል። መሰላሉ ላይ ከፍ ብዬ እየወጣሁ ነው። አያችሁ? በጎነትን፣ እውቀትን፣ ራስን መግዛትን፣ አሁን ደግሞ ትዕግስትን እጨምራለሁ። አሁንም ገና መንፈስ ቅዱስ አልተቀበልኩም።

279 ከዚያም ትዕግስት ከጨመርኩ በኋላ፡ እግዚአብሔርን መምሰል እጨምራለሁ። ያ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እንደ እግዚአብሔር። እጨምረዋለሁ። እራሴን ከአግባብ አላወጣም። እንደ ክርስቲያን ጨዋ ሰው እሆናለሁ። ያ-የተለጠፈ አይሁን። በእኔ ውስጥ የሆነ ነገር፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ብቻ ይፍለቅለቅ። አያችሁ? አያችሁ? “እ-እ-እ-እ፡ ይሄን ማድረግ እችላለሁ፡ ቢሆንም ማድረግ አልፈልግም፡” አትበል። አያችሁ? ኧ-ሃህ። ኧ-ሃህ። ምንም ቢሆን፡ አለ።

280 መወለድ ነው። የተወለድኩት **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ** ነው። ከዚያም የእግዚአብሔር ፍቅር፡ ክርስቶስ፡ ወርዶ በእኔ ያለውን ሁሉ፡ ለአገልግሎት ያትማል። አያችሁ?

281 ከዚያም መንፈስ ቅዱስን ሲሰጠኝ ምን ያደርጋል? ወደተለየው ሰፍራ ለብቻችሁ ይለያችኋል፡ ምልክት ያደርግባችኋል። አያችሁ? ያን ጊዜ ልዩ ሰው ትሆናላችሁ። ከእንግዲህ፡ የዓለም አይደላችሁም። አያችሁ? በተለየ መልኩ ለብሳችኋል። በተለየ መልኩ ለብሳችኋል። ይህ ውጫዊው ልብስ አይደለም። በጭራሽ፡ አይደለም። ያልተለመደ እና እንግዳ፡ አንገትጌውን ያዞረ፡ እና ረጅም ሰርዓት ፈጻሚ መሆን የለባችሁም። በጭራሽ፡ አይደለም። እንዲህ መሆን የለባችሁም። አካላችሁን፡ እንዲህ፡ ትለብሳላችሁ። አስፈላጊው መንፈሳዊ አለባበስ ነው። የሰርግ ልብስ በእናንተ ላይ ተደርጎላችኋል። እናንተ ምንድናችሁ?

282 ልክ እንደ ኢየሱስ፡ እነሆ፡ አንድ ነገር ሸፈነው፡ በዚያም በፊታቸው ተለወጠ፣ ልብሱም እንደ ፀሀይ ያበራ ነበር። እነሆ በዚያ፡ ኢየሱስ፡ እግዚአብሔር የራሱን ልጅ አኖረ። አያችሁ? ከዚያም ሙሴ ተገለጠ። ከዚያም ኤልያስ ተገለጠ። ጴጥሮስም፣ "ታውቃለህ፣ እዚህ መሆናችን ጥሩ ነው" አለው። የሰውን ነገር አያችሁ? አዎን። ኦህ፡ ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ነገር ተከሰቷል! እርሱም፣ "ሦስት ድንኳኖች እንስራ። አንዱን ለሙሴ፡ አንዱን ለኤልያስ፡ አንዱንም ለአንተ እንሥራ አለው።"

283 ንግግሩን ሳይጨርስ፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር አስቆመውና፡ እንዲህ አለ፡ "የምወደው ልጄ ይህ ነው። ይህን ሁሉ ከሙሴ የጠበቅኩት፡ በሙሴም የጻፍሁት ሕግ፥ ከነቢያትም በኩል ፍርድ ሁሉ፥ እሱ ሁሉንም አሟልቷል። እርሱን ስሙት። አሁን ከምስሉ ልውጣ። እርሱን ስሙት። እርሱን ስሙት።" ኦህ፡ ማይ! እንዴት ያለ የሚያምር ነገር ነው!

284 ከዚያም፣ እነዚህን መሰፈርቶች አሟልተን፡ በእግዚአብሔር ምግባሮች እና በእግዚአብሔር ነገሮች የተሞላን ስንሆን፣ ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በመንግስቱ ያትመናል። አታስቡ። ስታገኙት ሁላችሁ ታውቁታላችሁ። እንዲህ ማለት አይገባችሁም፡ "እንደው፡ ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን፡ እንዳገኘሁት አውቄአለሁ። በልሳን ተናግሬአለሁና። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡ እንዳገኘሁት አውቄአለሁ። በአንድ ወቅት አሸብሽቤአለሁና።" በዚህ ጉዳይ ምንም መናገር የለባችሁም። ስታገኙት ሁላችሁ ታውቁታላችሁ። አታስቡ። አዎን። ስለ ራሱ ይመሰክራል። ይህንንም በሰዎች መካከል ያስታውቃል።

285 እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ዛሬ ጠዋት ከእናንተ መካከል በመሆኔ፣ ይህን የኅብረት ጊዜ በማግኘቴ በጣም ደስተኛ ነኝ። ስሙኝ፡ ቤተ ክርስቲያናችን ትንሽ ናት፣ ቢሆንም እዚህ ለሚመጡት ሰዎች በቂ መቀመጫ የለንም። ድርጅት አይደለንም። ከእያንዳንዱ ድርጅት ጋር ህብረት እንዳለን እናምናለን። እዚህ መምጣት ስለፈለጋችሁ ብቻ ኑ። እናንተንም፡ እንወዳችኋለን። እኛ የምንፈልገው እያንዳንዱ ድርጅት፡ እያንዳንዱ ሰው...

286 በሁሉም ድርጅቶች ውስጥ ሰዎች ክርስቲያኖች እንዳሉ አምናለሁ። በክርስቶስ ወንድሞችና እህቶች ናቸው።

287 ስለዚህ፡ ክርስቲያን ከመሆን በቀር፡ ምንም ዓይነት ገመድ፣ የምንቀላቀለው፣ የምናደርገው ነገር የለንም። ኢ. ሆዋርድ ካድል፡ "ከፍቅር በቀር ህግ የለንም፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር የእምነት መግለጫ የለንም፡" ይል ነበር። ልክ ነው። ኑና ኅብኙን። ደስ ይለናል። ሙሉ ወንጌልን፣ እያንዳንዱን የቃሉን ነገር እናምናለን። በትክክል መንገዱን እናምናለን። በእሱ ላይ አንጨምርበትም፣ ማንኛውንም ነገር ከእሱ አንቀንስም፣ የማንኛውንም የድርጅት ነገር አንጨምርበትም። ልክ ባለበት ሁኔታ እንተወዋለን። ያ ነው። እና እርናንተን ለመቀበል ሁል ጊዜ ደስተኞች ነን። ስትችሉ ኑና ከእና ጋር ሁኑ። ለታመሙ ሰዎች እንጸልያለን። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ሁሉ እናደርጋለን ብለን እናምናለን። እነሆ እኛ "ድክመቶቻችንን፡ ወደ ኋላ እየረሳን፡ ከፍ ወዳለው የጥሪው ምልክት ለመድረስ እንዘረጋለን።"

288 አሁን፡ አንድ ተጨማሪ ነገር። እንዲባል ትፈቅዳላችሁን? ከትናንት ወዲያ በማለዳው... በዚያው በቦርዱ ላ—ላይ ታዩታላችሁ፡ ራዕይ ነው። ራዕይ አየሁ። ከኋላ ያለችው ባለቤቴ እንደምታውቀው፡ አምስት ሰዓት አካባቢ ነበር፡ ወይም ስድስት ሰዓት። ከእንቅልፌ ነቅቼ ነበር። ልጆቹን ለትምህርት ቤት ለማዘጋጀት ተነሳን።

289 እነዚህ ነገሮች፡ በየጊዜው ይደርሱብኛል። እና እዚህ ያላችሁ ሁላችሁም፡ በጭራሽ እንደማይወድቁ፡ ታውቃላችሁ። እነሱ፡ በሙላት ፍጹም ናቸው። አያችሁ? መቼም አይወድቁም።

290 እና ካየኋቸው ሁሉ ይልቅ በጣም ደስተኛ ሰው እንደሆንኩ አሰብኩ። እነሆ እኔ በፀሐይ ውስጥ ቆሜ ነበር፡ s-u-n፣ እ—እናም ወንጌልን ለትልቅ ግዙፍ ጉባኤ፡ እየሰበክሁ ነበር።

291 [ወንድም ብራንሃም ቆም አለ—እርታዒ።] እየተቀዳ መሆኑን ለማየት ፈልጌ ነው።

292 በ—በጣም ትልቅ፡ ግዙፍ ጉባኤ ነበር፡ ሰዎቹም ጫካ ውስጥ ተቀምጠው ነበር። በላያቸው ላይ የፀሐይ ጮራ እያበራባቸው ነበር፡ **እዚህ** እና **እዚያም**፣ ይቀበሉታል፣ ቃሉን ይቀበሉ ነበር።

293 እና፣ እንደተለመደው፣ ሁሌም እንደማስረዝም፣ በጣም እዘገያለሁ፣ ረጅም ሰበክሁኝ። ጉባኤው ሥጋዊ ምግብ እስኪራብ ድረስ፡ ብዙ ሰበክሁ። እና ከመካከላቸው፡ አንዳንዶች፡ ደከሙ። ስለዚህ ተነሥተው፡ የሚበሉትን ፍለጋ ወጡ፡ መውጣት ጀመሩ።

እኔም አልኳቸው፡ "አትውጡ። አትውጡ።"

294 ገና መዳሰስ የነበረብኝ ሁለት ጽንፎች ቀርተውኝ ነበር፡ በስብከቴ ውስጥ፡ መዳሰስ ፈለጌ ነበር። ይህም ጌታ ለእኔ ሰጠኝ። ማንኛውም ሰባኪ ያውቀዋል፡ በእውነት እግዚአብሔር የሰጣችሁ መሆኑን ስታውቁ፡ ለህዝቡ ለመናገር ያስቸኩላችኋል።

295 እና እኔ እየሰበክኩ ነበር፣ ቻርሊ፣ የቻልኩትን ያህል ጠንክሬ፣ በደንብ እየደረደርኩት፣ ታውቃላችሁ፣ እንዲህ እላቸው ነበር "እነዚህን ሁሉ ታላላቅ ነገሮች፣ **እነዚህ** እግዚአብሔር የሚያደርጋቸው። **ይህንን** ተመልከቱ። እርሱ የልብን አሳብ ያውቃል። ይህ ምንድነው? ቃሉ።" እና እንደዛ ቀጠልኩ። እና፡ ኦህ፡ ንግግሬን እና ርዕሰ ጉዳዬ ምን እንደነበረ ባስታውስ እንዴት ደስ ባለኝ። አላስታውሰውም። አያችሁ? ብቻ ግን በሙሉ ኃይሌ ሰበኩኝ።

296 እኔ ራሴ ያንን ሳደርግ እራሴን አየሁ። እናም እዚያ ቆሜ፡ እየተመለከትኩ ሳለሁ፡ ያንን እየሰበኩ ራሴን አየሁ።

297 እና እንደው-ለ-ለማይቀበሉት-ሁሉ-እንዲሁ፡ ሰበክሁላቸው። ትንሽ ቆይቼ፣ ቆምኩኝ፣ ታውቃላችሁ፣ "እግዚአብሔር ይመስገን፡" ብዬ አሰብኩ! "እነዚህን ሁሉ አስደናቂ ነገሮችን፣ **ይህም**፣ **ያም** ተመልከቱት!" አልኩ።

298 ወዲያውም፡ ሰዎች ለሥጋዊ ምግብ የተራቡ መስለው መታየት መጀመራቸውን በድንገት አስተዋልኩ። በቂ መንፈሳዊ ምግብ ስለነበራቸውም፡ መሄድ ጀመሩ። አንዳንዶቹም [ወንድም ብራንሃም ማዛጋትን አስመሰለ—እርታዒ።] መሄድ ጀመሩ።

እኔም፡ “ሰዎቹ ምን ነካቸው? ” አልኩት።

299 እ—እና አየሁም፣ አንዳንድ ወጣት ጥንዶች፡ በአጠገቤ ሲያልፉ ነበር። አሰበኩና... እንዲህ አልኳቸው፡ “ወዳጆች ሆይ፡ እንዴ ጠብቁኝ! እንዴ ብቻ! የምሽት ጥቁር ድባብ ሲወርዱ ተመልሳችሁ ትመጣላችሁ።” አያችሁ? እንዲህ አልኳቸው፡ “ተመልሳችሁ ትመጣላችሁ። ቢሆንም አንደኛውን ጽንፍ ልሰጣችሁ። ይህም የእነዚህ ያሳየኋችሁ ነገሮች ሁሉ፡ ምንጫቸው ምንድነው? ከምን ናቸው? ” እንዲህም አልኩኝ፡ “ይኸው እነዚህ ናቸው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አሉ። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ናቸው፡ ተሰፋው ናቸው። ምክንያቱም፡” “ሁላችሁም ትመሰክሩልኛላችሁ፣ ተልእኮዬም ‘በቃሉ ኑሩ’ እንደሆነ ምስክሮች ናችሁ፡” አልኳቸው። “እናንተ ሁላችሁ ምን ነካችሁ? ቃሉን መረዳት አትችሉምን? መረዳት አለባችሁ፡” አልኳቸው።

300 እና አንዳንዶቹ፡ “አንተ ሰው፡ ብሰኩት ነገር ባገኝ ደስ ይለኛል፡” ወዘተ ይሉ ነበር።

301 እንግዲህ፡ “መልካም ነው፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! ብሰኩት ከፈለጉ፡ ይሂዱና ያግኙ፡” ብዬ አሰብሁ።

302 ስለዚህ ዘወር እ—አልኩ። እኔም “ኡህ፡ ግን’ኮ፡ ታውቃለህ? ጥቁር ድባብ፡ ከአፍታ በኋላ፡ ቶሎ ይወርዳል፡” ብዬ አሰብሁ። እንዲህም አልኩ፡- “ታዲያ፡ ዛሬ ማታ፡ ይህ ጉባኤ እንደገና ሲሰበሰብ፡ የመጨረሻውን ጽንፍ አስቀምጥላቸዋለሁ፡ እኔም ሳደርግ ያዩት ነገሮች የሚገኙት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንጂ፡ በአንዳንድ አፈ ታሪኮች ወይም አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ አይገኙም። በቃሉ ውስጥ ይገኛሉ። አያችሁ? የተቀበልኩት ተልእኮ ነውና፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች፡ በቃሉ ውስጥ አሉ ብዬ እነግራቸዋለሁ።”

303 እንዲህ አሰብሁ፡ “ይኸውልህ፡ እነዚህ፡ ሁሉም፡ ዛሬ ማታ ይመለሳሉ፡ እና እኔ የማደርገው ይኸው ነው። እንደገና ዳራውን፡ ዳራውን እሰራለሁ።” እንደምታውቁት በቤተ ክርስቲያን ዘመናት እና በሁሉም ነገር እንዳደረግኩት፣ አስቀድሜ የተናገርኩትን እደግማለሁ። “ዳራውን፡ ከቃሉ እወስዳለሁ፡ ከዚያም ይህን የከበረ፡ አስደናቂ ጽንፍ አቀርባለሁ።” እኔም፡ “እንዴት ያለ ጊዜ ይሆናል! ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!” እናም እኔ ራሴን በጣም ትንሽ ሆኜ አየሁት፣ እናም ይህን “ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡” ሰማሁ። ራሴን **እንደዛ** እየደበዘዘ ሲሄድ አየሁ። ከዚያ በኋላ፡ እነሆ እዚሁ ቆሜ ነበር።

304 አሁን፣ የዚያ ትርጓሜው ይኸው ነው። አያችሁ? መጀመሪያ ያደረግኩት፣ እነዚያ የተከናወኑት ነገሮች፣ ለሰዎች፣ ለአብዛኞቹ ምሥጢራዊ ነበሩ። አሁን የምናገረው፡ ስለ ሙሉ ወንጌል ሰዎች፡ እና ስለ እግዚአብሔር ቅዱሳን ሳይሆን፡ ስለ አብዛኛው ሰው ነው። እና ዓለምን፣ ኮሰሞስን፣ የእግዚአብሔር መልእክት እንደሆነ አድርገን ልንቆጥረው አይገባም። ወጥታችሁ እንዲህ ስትሉም...

305 ቦዜ እንዳለው፣ “እኔ ሁልጊዜ... ” አለ፣ “ከዓመታት በፊት በሕልም፣ እግዚአብሔር ወደ ቺካጎ እንደሚልከኝ እና ቺካጎም ለእግዚአብሔር ክብር እንደምትናወጥ፡” አየሁ አለ።

እኔም “ጆሴፍ ሆይ፡ ካናወጣት ቆየ፡” አልኩት።

“ለምን፣” “ከሙዲ ጀምሮ አልተናወጡም፡” አለ።

306 እኔም፡ “ያንን? የማወራው ስለ ቤተክርስቲያን ነው። የእሳት ራት ናቸው። የተቀባቡ እና አሸንክታባሞች ኤልዛቤሎች ሁሉ፡ ጎዳናውን የሚያጨናንቁ፡ እነዚህ የሞድር ትቢያዎች ናቸው።” “በዚያ ያሉ አሉ። ታላላቅ ማሕበራዊ እድሮች እና መሰሎቻቸው፡ ጎዳናው ላይ ተንከባለው ይወድቃሉ፡” አልኩት። እኔም፡ “እሱ እየተናገረ ያለው ስለ ቤተክርስትያን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ አይታ፡ እና ያወቀች ቤተ ክርስቲያን። ከቺካጎ አሥራ አምስት ላይሆኑ ይችላሉ። በዚህ ትውልድ ውሰጥ፡ ከመላው የቺካጎ ከተማ የሚወጡ፡ አሰር ላይሆኑ ይችላሉ።”

307 ይህን ነገር አሰባችሁት ታውቃላችሁ? “ሰምንት ሰዎች እንደዳኑበት፡ በኖኅ ዘመን እንደነበረ፡ የሰው ልጅ በሚመጣ ጊዜም እንዲሁ ይሆናል።” ኧሃ-ሃህ። ከሰዶም ሰንት ወጡ? ምን ማለቴ እንደሆነ አይታችኋል? እፍኝ ከወጣ እጠራጠራለሁ። አያችሁ?

308 ነገር ግን ቤተክርስቲያን ራሷ መነቃቃቱን ተቀብላለች። አውቀውታል። ቃሉን ያውቁታል። ቃሉ ሲፈጸም አይተውታል፡ ተቀብለውታል። አሁን ያንን ለአንድ ደቂቃ ተመልከቱ፡ አሁን።

309 እንግዲህ፡ የመጀመሪያው መልእክት፡ ባዩት ጊዜ፡ ሁሉም በዙሪያው ተሰበሰቡ፣ እንዲህም አሉ፣ “ኦህ፣ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! ኦህ፣ **ይህን፣ ያንን፣** እና **ሌላውን** ማየት ከቻልኩ” ይሉ ነበር። እና ልክ እንደአገባባቸው፡ እንዲሁ እንደገና ወጡ። አያችሁ?

310 ከዚያም እንዲህ አሰቡ፡ “እንጃ፡ እኔ አላውቅም። የየትኛው አባል ትሆናለህ? **ወደዚህኛው** ካልገባሁ፡ **እንዲህ** ይሆንብኛል። እዚህ ጋር ደግሞ፡ ያባርሩኛል፡ **ከዚህ** ጋር ምንም የለኝም።” ወንድሞች ተቀመጡና እንዲህ በሉ፡ “እንጃ፡ እኔስ ይህ ሲሆን ምን አደርጋለሁ... ? ” አያችሁት? እግዚአብሔር የገባውን ቃል፡ እራሱን እየገለጠ መሆኑን ለማወቅ በበቂ ሁኔታ መታገስ አልቻሉም። አያችሁ? ትተው ሄዱ።

311 ይሁን እንጂ፡ አትታወኩ፡ ድባቦች በደጅ ቀርበዋል፡ አያችሁ፡ እነሆ እኔ ወደ መሰኩ በተመለሰኩ ጊዜ።

312 ታስታውሳላችሁ፡ በቀደም ማታ፡ የማዕዘን ድንጋዩን ሳሰቀምጥ በዚያ ሰለ ነገረኝ መልእክት ባለፈው የነገርኳችሁን ታስታውሳላችሁ? በትክክል። እርሱም፡ “ሥራውን ሥራ... ” አለኝ፡ “ከዚህ ራዕይ ሰትወጣ፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4ን አንብብ። ይኸውልህ፡ ከሠላሳ-ሦሰት ዓመታት በፊት፡ በዚያ የማዕዘን ድንጋይ ውሰጥ አለ።

313 እንዲህ ይላል፡ “የወንጌል ሰባኪነትን ተግባር ሥራ፡ አገልግሎትህን በመልካም ፈጽም። ሰዎች ጤናማ ትምህርት የማይታገሡበት ጊዜ ይመጣልና፥ ነገር ግን ከተረት... ከእውነት ወደ ተረት በመመለስ፡ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ሰለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ።” ቃል በቃል፡ ነገሩ ያ አይደለም ወይ! [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]

314 ግን፡ አሰታውሱ፡ ደግሞ፡ በቀደም ምሽት፡ ሳነብላችሁ እሰከመጨረሻው አላነበብኩትም። በዚህ ድንኳን ውሰጥ የሰበኩባቸው ሰላሳ-ምናምን ዓመታት፣ አንድም ቀን ከዚያ በላይ ሄጄ አላውቅም፣ እና ለምን እንደሆነ አላውቅም።

315 ኢየሱስ ጥቅሉን ይዞ፡ የትንቢቱን ግማሹን አንብቦ ቆሞ ማንበብ የጀመረበትን፡ ምንባብ፡ እስካየሁበት ቀን ድረስ፡ ይህን ጥያቄ ለራሴ፡ ብዙ ጊዜ፡ እጠይቅ ነበር፡ በዚያ በቅፍርናሆም፡ "ይህ ትንቢት፡ ዛሬ ተፈጸመ፡" አላቸው። ሌላውን ለምን አላነበበውም? ይህ ሰለ ዳግም ምጽአቱ የሚመለከት ነው። እያችሁ?

316 በዚያም፡ ሳልረዳው ያንን አንብቤዋለሁ። ያንን ጽሑፍ ወሰጄ፡ እነሆ እዚያው በደቡባዊ ፓይን፡ ደቡብ ካሮላይና ውስጥ፡ ከፊት ለፊቴ ነበር። የዛን ቀን ጠዋት ወጥቼ፡ ከጆሴፍ ቦዜ ጋር፡ ከመኪናው ጎን ተደግፌ፡ እየተነጋገርኩ ነበርኩና፡ መታ አደረግኩ። [ወንድም ብራንሃም ጣቶቹን አንቃጨለ—እርታዒ።] ጳውሎስ ሲናገር፡ "እነሆ... ሁሉም ትተውኛል። ብቻዬን ሆኛለሁ። ዴማስ የአሁኑ ዓለም ወዶ፡ ትቶኛል። አሁንም እኔ... " ተመልከቱ። "እንጥረኛውም በብዙ ጎዳኝ።"

317 ዴማስ ምን አሰቦ ሊሆን እንደሚችል እዩ፡ "እሺ፣ ጳውሎስ ወንጌልን ሲሰብክና የታመሙትን ሲፈውስ አይቻለሁ። ቢሆንም፡ እነሆ እሱ ራሱ፡ እየተሰቃየ ነው፡ ከእሱ ጋር ዶክተር ሉቃስን ይዞ ይመላለሳል። በሄደበት ሁሉ፡ መለኮታዊ ፈውስን የሚሰብክ ሰው፡ እነሆ ዶክተር ይዞ ይሄዳል። እንግዲህ፡ ሰውን ሲያሳውር አይቼው አውቃለሁ። እርሱንም 'እግዚአብሔር ይገሰጽህ ለጊዜው ዕውር ትሆናለህ፡' ብሎ ነበር። እንጥረኛውንም ከሰብሰባው አባርሮ ነበር። አሁን ሰዎችን የሚያሳውርበትን ኃይል ያጣ ይመሰለኛል። እነሆ፡ ወዮ፣ መለኮታዊ ፈውስ ኃይሉን አጥተዋል። እግዚአብሔርም ከእርሱ ዘወር ብሏል።"

318 ዴማስ ወደ አለም የሄደ አይመሰለኛም፣ ምክንያቱም ዴማስ የ ሀ... ታሪኩን ታውቃላችሁ። እሱ የመጣው ከአንድ ትልቅ እና ሀብታም ቤተሰብ ነው። እና እሱ ከሌሎች ጋር መሄድ ፈለገ።

319 ነገር ግን፡ ጳውሎስ ግን፡ ምሰኪኑ ጳውሎስ። ምን ነበር? እግዚአብሔር ሁል ጊዜ አንድን አገልግሎት እንደዚያ እንዲሆን ያደርገውና ከዚያም አክሊልን ያደርግበታል።

320 ኢየሱስን ዝም ብሎት ያውቃል። ተመልከቱት። ሙታንን ማስነሣት እየቻለ፡ የፈለገውን ማድረግ እየቻለ፥ አንድ ሮማዊ ወታደር ጢሙን እንዲነጭ፡ እና ፊቱ ላይ እንዲተፋበት ፈቀደ። [ወንድም ብራንሃም የመትፋት ድምፅ አሰማ—እርታዒ።] ደጋግሞ መታው... ፊቱ ላይ ጨርቅ ሸፍነው፡ እንዲህ አሉት፡ "አሁን፡ ይኸውልህ፡ ነብይ እንደሆንክ ነግረውኛል።" ሁሉም ዱላቸውን ይዘው ከበውት ቆመዋል፡ ጭንቅላቱንም ይመቱት ነበር። [ወንድም ብራንሃም የሆነ ነገር መታ።] "እሺ፣ ማን እንደመታህ ንገረን" አሉት። ማን እንደመታው ያውቃል። ኧሃ-ሃህ። በእርግጠኝነት። ያውቃል። አያችሁ? አገልግሎቱ ግን ዘውድ ሊቀዳጅ እየተዘጋጀ ነው።

321 እና በአብዛኛው ጊዜ እጅግ፡ እጅግ ደካማ፡ የጠፋ እስኪመሰል ድረስ ያደርሰውና፡ ያኔ እግዚአብሔር ዘውድ ይጭንበታል።

ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ።

ራሶቻችን ዝቅ እናድርግ።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ

ቀድሞ ሰለ...

አሁን አምልኩት። ከባድ ትምህርት ተምረናል።

መዳኔንም ገዝቷል
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

322 አሁን እጆቻችንን ወደ እርሱ እንዘርጋ።

እ...

አሁን በመንፈስ ሁኑ፡ እሺ፡ "እወደዋለሁ።"

... እወደዋለሁ
ቀድሞ ሰለወደደኝ።
መዳኔንም ገዝቷል
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

323 አሁንም፡ በእግሮቻችን፡ እንቁም።

በትንሽ የማሰናበቻ መዝሙራችን፡ የመጀመሪያውን አዝማች እንዘምራለን፡ እርስ በእርሳችን እንጨባበጣለን፥ ሁለተኛው አዝማች ለእግዚአብሔር እንዘምራለን። እሺ። ከዚያ በኋላ እንዘጋለን።

አሁን፣ እንዘምር፦

የኢየሱስ ስም ከአንተ ጋር ይሁን፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
ደስታ እና ምቾት ይሰጣል፡
በሄድክበት አትለየው።

ድንቅ ሰም፡ ኦህ ውድ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ሰም፡ ኦህ ውድ ነው!
የምድር ተስፋ... የሰማይ።

324 አሁን፡ ይህንን አስታውሱ፡ አሁን። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ክፍል ውስጥ ያገኘሁት፡ አንድ ምስኪን ወንድማችን፡ እሱን ወደዚህ እጋብዛለሁ፥ እ—እጅግ ድንቅ ወንድማችን፡ እዚያ በበረሃው ያለውን የአሴምብሊ ሚሽነሪ ነው፥ ሰሙን ረስቼዋለሁ፡ ሁለተኛውን አዝማች ስንዘምር፡ እርሱ መጥቶ ጉባኤውን በጸሎት እንዲዘጋልን እጠይቀዋለሁ፥

የኢየሱስ ሰም ከአንተ ጋር ይሁን፡
ወጥመድ ሲኖር ይታደጋል፡
ፈተና ሲበዛ ሁከት ሲሆን ዙርያህ፡
ቅዱስ ሰሙን ተንፍስ በጸሎትህ።

325 ከዚያ ሰይጣኖች ሲወጡ ታያላችሁ። አያችሁ? አሁን፡ አስታውሱ፦

የኢየሱስ ሰም ከአንተ ጋር ይሁን፡
ወጥመድ ሲኖር ይታደጋል፡
ፈተና ሲበዛ ሁከት ሲሆን ዙርያህ፡
ቆም በልና፡ ቅዱስ ሰሙን ተንፍስ በጸሎትህ።

326 ምን እንደሚከሰት ተመልከቱ። እሺ። አሁን በአንድነት።

የኢየሱስ ስም ከአንተ ጋር ይሁን፡
ወጥመድ ሲኖር ይታደጋል፡
ፈተና ሲበዛ ሁከት ሲሆን ዙርያህ፡ (ያኔ፡ ምን ታደርጋለህ? )
ቅዱስ ስሙን ተንፍስ በጸሎትህ።
ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም) ኦህ ውድ ነው! (ኦህ ውድ ነው!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ… ፡ (… ? … ያቺ ብላቴና ተመልከቷት… ? … ) ኦህ ውድ ነው! (ወደዚህ ነይ የኔ ማር።)
ተስፋ…

327 እዚህ እንደቆማችሁ፥ ባለፈው እዚህ ተበርናክል በነበርኩ ጊዜ፡ እዚህ ጋር (ይህች እናት በዚህ ህጻን ላይ እየጠቆመች ሰትሰቅ ነበር።)፡ ይህ ህጻን ብረት ተገጥሞበት ነበር። እነሆ፡ ዛሬ፡ ላይ ታች እየተሯሯጠ በደንብ እየተጫወተ ይገኛል። ደስ አይልምን? ጌታ ይባረክ። አሁን፡ ተመልከቱት፥ የኔ ማር፡ እዚያ ጋር፡ ወደ ታች ዝለልና፡ መሮጥ እንዴት እንደምትችል እስኪ አሳያቸው። እሺ?

ኦህ፡ ድንቅ ስም፡ (እንግዲህ፡ የዛሬ ምሽት የጌታ እራት እንዳትረሱ።)… ውድ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ ኦህ ውድ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ…

328 አሁን አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። እና የዛሬ ማታ ፕሮግራም እንዳንረሣው፡ ይህም፥ የጌታ እራት ምሽት ነው። እናንተ፡ ክርስቲያኖች የሆናችሁ፡ ሁላችሁም አስታውሱ፡ መጥታችሁ ከእኛ ጋር የጌታ እራት ለመካፈል ጋብዘናችኋል። ጥሩ ጊዜ ይሆንልናል።

329 ይህ፡ የተወደደው ፓስተራችን፡ ወንድም ኔቪል፡ እና… ሰንቶቻችሁ ወንድም ነቪልን ትወዱታላችሁ? "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ወንድሞች ሆይ፡ ሰሙኝ፡ እኔን እንደ… በተበርናክሉ ካሉት ፓስተሮች እንደ አንዱ ሰሙኝ፡ ከወንድም ኔቪል ጋር ተጣበቁ። ከእርሱ ጋር ሁኑ። አያችሁ? እርሱ የክርስቶስ አገልጋይ ነው። ከእርሱ ጋር ሁኑ። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ "ይልቁንም ይህ ክፉ ቀን ሲቀርብ እያያችሁ፡ በአንድነት ሕብረት እንሰብሰብ" ይላል። ጉባኤ ላይ ተገኙ፡ ኑ፥ በቅን እየሄድን ከፓስተራችን ጎን እንሰለፍ። እሺ? በአግባባ እንጽና…

62-1104M የተሰደቡ ሰዎች
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2025 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org